አማራ ኮሙኒኬሽን ቢሮ



# ሐዲስ

ታህሳስ 2018 ዓ.ም

20ኛ ዓመት ቁጥር 67




“የህዳሴው ግድብ የትውልዶች ህልም በልዩ ጀግንነት እውን የሆነበት ዘመን ተሻጋሪ ሰነድ ነው።”

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሰት
የመንግስት ኮሙኒኬሽን ቢሮ

## ርዕይ

በመረጃ የበለፀገ፣ ሁለገብ ተሳትፎ የሚያደርግ፣ በመሠረታዊ ክልላዊና አገራዊ ጉዳዮች መግባባት የፈጠረ ህዝብ በ2022 እውን ሆኖ ማየት

## VISION

To see a society with rich information and all rounded active participation for a better understanding on fundamental regional and country level affairs for having common consensus in 2030

## ተልዕኮ

በመንግስት ኮሙኒኬሽን ኢንፎርሜሽንና ሚዲያ ዘርፍ መሪ ሚና በመጫወት በህብረተሰቡ መካከል ውጤታማ የመረጃ ልውውጥ በማድረግ በመሰረታዊ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች፣ ዕቅዶችና ኘሮግራሞች ዙሪያ የመላውን ህዝብ ግንዛቤ በማዳበር ሁለንተናዊ እድገታችንን ወደ ላቀ ደረጃ በማሸጋገር ለራዕያችን ስኬታማነት የተቀናጀ ርብርብ ማድረግ፣

## MISSION

playing a leading role in government communication information for a successful information exchange with in a society. to enhance the awareness of the people on the fundamental government policies strategies. plans and programs for a better step of succession our vision by stron collaboration.

# ሐዲስ

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የመንግስት ኮሙኒኬሽን ቢሮ በየ 3 ወሩ የሚዘጋጅ መጽሔት

20ኛ ዓመት
ቁጥር 67

ታህሳስ ወር
2018 ዓ.ም

አዘጋጆች

ህያው ተስፋዬ
ይበልጣል መኮነን
ሲሳይ ጌቴ
ደፋሩ እምሬ
ሳሮን ስማቸው

አርታኢ

ጋርዳቸው አንሙት
ፈቃዱ ገድፍ አስናቀ

ህትመት ስርጭትና ክትትል

ደባሱ ካሣ

ግራፊክስ ዲዛይን

ጌታሁን ላቀ

ማውጫ ገጽ

ደብዳቤዎች ........................................2

መልዕክቶች ........................................3

ፖለቲካ/መልካም አስተዳደር

ሪፎርም ለላቀ ውጤት!! ...................4

ልማት/ኢኮኖሚ

የትውልድ ህልም ...............................8

ባህል/ ታሪክ

ዋጋው የላቀ........................................13

ማህበራዊ

"ሜዳውም ያው…" .........................17

ልዩ ልዩ

በጉነት...................................................23



## ውድ አንባቢያን መጽሔታችንን በማንበብ አስተያየታችሁንና መልዕክቶቻችሁን በሚከተሉት አድራሻዎቻችን ይላኩልን


- **Facebook** Amhara Communications
- **ኢሜል** anrsnproduction@ gmail. com
- **ዩቲዩብ** Amhara Communications
- **ቲውተር** @ANRSGCAO
- **ዌብሳይት** www.amharacomm.gov.et
- **ስልክ** 058 220 09 40 ፣ 058 226 5921፣ 058 220 4107
- **ፋክስ** 058 220 1105 / 058 226 4172
- **ፖ.ሣ.ቁ** 607

# ሰላማችንን በማፅናት የብልፅግና ጉዞአችንን እናፋጥናለን!!

በሀገር ግንባታ ውስጥ በርካታ አኩሪ ታሪኮች ያሉት የአማራ ህዝብ ከክልሉ ባለፈ የሀገራችን ህዝቦች ቋንቋቸው፣ ሃይማኖታቸው፣ ማንነታቸውን ጨምሮ ልዩ ልዩ ባህላዊ ዕሴቶቻቸው ተከብረው እንዲኖር በደምና አጥንቱ ጭምር በርካታ መስዋዕትነትን የከፈለ ታላቅ ህዝብ ነው፡፡

ባለፉት የለውጥ አመታትም ኢትዮጵያዊ የሆነ ሁሉ ሡብዓዊና ዴሞክራሲያዊ የሆኑ መብቶቹ ተከብረውለት በነፃነት እንዲኖር የክልሉ መንግስት እና ህዝብ ሠፊ የሆነ ርብርብ እንዳደረጉ ይታወቃል፡፡

በተለይም በተሳሳተ ትርዕክት ህዝባችንን ዋጋ ሲያስከፋሉ የቆዩ ግፈኞችን ከሌሎች የሀገራችን ብሄሮች ብሄረሰቦችና ህዝቦች ጋር በመተባበርና በተለይም በአማራ ወጣቶችና ሌሎች የማህበረሠብ አባላት ትግል የለውጥ አየር በኢትዮጵያ ምድር እንዲመጣ ግንባር ቀደም መስዋዕትነት ተከፍሏል፡፡ በለውጥ ኃይሎች የተባበረ ክንድና በህዝብ ደጀንነትም ለውጡን ማስቀጠል ተችሏል፡፡

ይሁን እንጂ ይህን የለውጥ ጅማሮ ለመቀልበስ በተለያዩ አቅጣጫዎች በርካታ ፈተናዎች አጋጥመውናል፡፡ በሴራ ፖለቲካ ተወልደው ያደጉ ባንዳዎችና ፅንፈኞች በውጭ ታሪካዊ ጠላቶቻችን እየታገዙ ሀገራችንንና ክልላችንን በጦርነት ለማመስ ተረባርበውብናል፡፡ በተለይ በክልላችን በፋኖ ስም በሚነግዱ ጽንፈኛ ቡድኖች በክልሉ ህዝብ ላይ ሰባዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳት አድርሰዋል፡፡ ነገር ግን መንግስት ከታታሪው፣ ከአርቆ አስተዋዩና የንሥር ዓይን ከታደለው ህዝባችን ጋር በመሆን በሆደ ሠፊነት የገጠሙትን ችግሮች ሁሉ ተቋቁሞ እንደ ክልል በልማት፣ በሰላምና በልዩ ልዩ ተግባራት በተለየ እምርታዊ ጉዞ ውስጥ ለመግባት ጥረት አድርጓል፡፡ ተጨባጭ ለውጥም ማስመዝገብ ተችሏል፡፡

በክልላችን የተፈጠረው የሽብር ተግባር የውስጥና የውጭ ጠላቶቻችን በተቀናጀ መልኩ ኢትዮጵያን ለማፍረስ አማራውን በልዩ ልዩ መልኩ ማዳከም በሚል የሚከተሉት እቅድ መሆኑ በግልጽ ሁሉም ሊያውቀው  ይገባል፡፡ ይኸ እቅድ የጦር መሣሪያ በማስታጠቅ፣ በፋይናንስና በሚዲያ በተቀናጀ መልኩ ታስቦበት የተሠራና የአማራን ህዝብ አንድ እንዳይሆን ለማድረግና እርስ በርስ እንድንባላ የተሸረበ ደባ ነው፡፡

ስለዚህ አማራን በሁሉንተናዊ መልኩ የማዳከም ፕሮጀክት ያላቸው ባንዳዎችንና ባዳዎችን ጀግናው የመከላኪያ ሰራዊታችንና የክልላችን የፀጥታ መዋቅር አስፈላጊውን ዋጋ ሁሉ በመክፈል የክልሉን ሰለማ በማረጋገጥ ላይ ይገኛል፡፡  ከምንም በላይ የተጀመረውን የልማትና የብልጽግና ጉዞ በማስቀጠል የአማራን ህዝብ ሁለተናዊ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ አክራሪነትና ፅንፈኝነት ለማንም የማይበጅ የተሸናፊዎች መንገድ በመሆኑ ችግሮችን በውይይትና በሰላም ለመፍታት የክልሉ መንግስት ዝግጁ መሆኑን ያረጋግጣለን፡፡

በአጠቃላይ መንግስት ከህግ ማስከበሩ ጎንለጎን የተገኘውን አንጻራዊ ሰላም ወደ ዘላቂ ሰላም ለማሸጋገር በተለያየ ቦታ ካለው ቡድን ጋር በተቻለ መጠን ተደጋጋሚ ውይይቶችን ማድረግ እና በክልሉ የልማት ሥራዎችን ማስቀጠል ክልሉ በትኩረት የሚሠራበት ጉዳይ ነው፡፡ በተለይ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የአጭርና የረዥም ጊዜ ስትራቴጅክ ዕቅድ በማዘጋጀት በግብርና፣ በኢንዱስትሪ፣በማዕድንና ቱሪዝም ልማት ዕምርታዊና ተመጋጋቢ ዕድገት በገጠርና በከተማ ለማስመዝገብ ዓልሞ በመስራት ላይ ይገኛል፡፡ እየተመዘገቡ ያሉ ተስፋ ሰጭ የልማት ውጤቶችም አሉ፡፡ ለአብነትም የከተሞች የኮሪደር ልማት፣የማንፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ልማት፣የታላቁ የህዳሴ ግድብ ግንባታ መጠናቀቅ፣የስሚንቶ ፋብሪካዎች ወዘተ.በቂ ማሳያዎች ናቸው፡፡

ከሥራ አጥነት እና ከኑሮ ውድነት ጋር ተያይዘው ከሕዝባችን የሚነሱ ችግሮችንም ለመፍታት  ከመቼውም ጊዜ በላይ በአገልጋይነት መንፈስ ጠንክረን እየሰራን እንገኛለን። በመሆኑም ዘላቂ ሰላምን እና ልማትን ለማረጋገጥ በሚደረገው ትግል ሕዝቡ ድጋፉን አጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል፡፡ በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንም በተለይም የአማራ ተወላጆች በሐሰተኛ መረጃዎች ሳይደናገሩ በክልሉ ሰላም እንዲሰፍንና የልማትና የብልጽግና ጉዞአችን እንዲረጋገጥ በምናደርገው ርብርብ ተሳታፊ እንዲሆኑ ጥሪያችንን እናቀርባለን፡፡

**የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት**

# ሪፎርም ለላቀ ውጤት!

በሲሳይ ጌቴ

የመንግስት አገልግሎትና አስተዳደር ዘርፉ በህግና በአሠራር ሥርዓት መመራት የተጀመረው በ1950ዎቹ ጀምሮ ቢሆንም ግልጽነትና ተጠያቂነት የሰፈነበት አተገባበር ላይ ግን ውስንነቶች ነበሩ፡፡ ከዚያም በመቀጠል ቀጣዮቹ ሥርዓቶች ነባሩን ሲቪል ሰርቪስ ከማስቀጠል ውጪ ከማዘመን አኳያ የወሰደው እርምጃ አልነበረም።

ከ1994 ዓ.ም ጀምሮ መንግስት ከነባሩ የፖሊሲ ለውጦች ጋር የተጣጣመ የመንግስት ሠራተኞች አስተዳደር ለመፍጠር የሚያስችል የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራም ቀርጾ ተግባራዊ ሲያደርግ ቆይቷል፡፡ ይሁን እንጂ የመንግስት መስሪያ ቤቶች በርካታ ሠራተኞችን በመቅጠር የሠራተኞችን ቁጥር ከማሳደግ ውጪ የመፈጸም አቅምን በመገንባት ረገድ የሚፈለገውን ያህል ውጤት ማምጣት ሳይቻል ቆይቷል፡፡

በዚህ ምክንያት የሰው ኃብት አስተዳደሩም የሥነ-ምግባር እሴቶችን፣ የሰው ኃብት ምልመላና መረጣ፣ የሙያ ዕድገት መሰላል፣ የደመወዝና ጥቅማጥቅም ሥርዓት እና የሥራ አካባቢ ለሠራተኞችና ለተገልጋይ ምቹ ከማድረግ አኳያ በሚፈለገው ደረጃ አልደረሰም፡፡

የመንግስት ተቋማት የሚጠበቅባቸውን ቀልጣፋና ውጤታማ አገልግሎት መስጠት እንዲችሉ የመንግስት ሰራተኞች አስተዳደር መዘመን እና በቀጣይነት በተጠያቂነት መርሆች መመራት አለበት፡፡

ይሁን እንጅ ሀገሪቱ ያለችበትን ወቅታዊ ሁኔታ መረዳትና ዘመኑ ከሚጠይቀው ፈጣን ለውጥ ጋር የተጣጣመ ዘመናዊ የሰው ሀይል አስተዳደር መገንባት ያስፈልጋል፡፡ በመሆኑም ከዚህ አኳያ ለውጥ ዕውን ለማድረግ ውጤታማና ተወዳዳሪ ሀገራዊ የመንግስት አገልግሎትና አስተዳደር መገንባት የሚያስችል ሪፎርም ያስፈልጋል፡፡



**አቶ እንዳላማው ልመንህ**
የሪፎርም ድጋፍና ክትትል
ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር

የሚያስችል አዲስ የመንግሥት አገልግሎት አስተዳደር ሪፎርም ነድፎ ተግባራዊ ማድረግ ይገባል፡፡ ሪፎርሙም በዋናነት በመንግስት መስሪያ ቤት ውስጥ ውጤታማና ተናባቢ የሆነ የተቋማት አደረጃጀት፤ ብቃትና ተነሳሽነት ያለው በስነ-ምግባር የታነጸ የሰው ሃብት ማፍራት የሚያስችል ነጻና ገለልተኛ የሰው ሃይል ስምሪት በማካሄድ ውጤታማ የመንግስት አገልግሎትና አስተዳደር ተቋም መፍጠር ያስፈልጋል ፡፡ ስለዚህ ይህን ውጥን ተግባራዊ ለማድረግ መንግስት ከያዝነው በጀት አመት(ከ 2018 ዓ.ም.) ጀምሮ ተግባራዊ የሚሆን የመንግስት አገልግሎት እና አስተዳደር ሪፎርም ጀምሯል፡፡

የሐዲስ መጽሔት ዝግጅት ክፍልም በአማራ ክልል ሲቪል ሰርቪስ እና የሰው ሃብት ልማት ቢሮ በመገኘት በመንግስት አገልግሎትና አስተዳደር ሪፎርም እንዲሁም መሶብ የአንድ ማዕከል አገልግሎት ዙሪያ ከሪፎርም ድጋፍና ክትትል ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ከሆኑት ከአቶ እንዳላማው ይታይህ ጋር ያደረግነውን ቆይታ እንደሚከተለው አዘጋጅተነዋል፡፡ መልካም ንባብ!!

አቶ እንዳላማው ወደ ሪፎርም ትግበራ እንዲገባ በርካታ መነሻ ምክንያቶች እንዳሉ ይገልፃሉ፡፡ ለአብነትም የክልሉ የተቋማት አደረጃጀት በየደረጀው ካለው ከፌዴራል ተቋማት ጋር ተናባቢ አለመሆን ነው፡፡ የክልላችን የተቋማት አደረጃጀት የአካባቢውን የመልማት አቅምና የህዝብ ብዛት መሰረት ያደረገ አልነበረም፡፡ የተቋማት ተግባርና ኃላፊነት የተደበላለቀ መሆን፣ ከተሰጣቸዉ ተልዕኮ አንጻር ተጠሪነታቸውን ጠብቀው ተቋማት አለመደራጀት እና ተቋማት ለአግልግሎት ሰጭው ሰራተኛም ሆነ አገልግሎት ፈላጊው ህብረተሰብ ምቹ አለመሆናቸው ነው፡፡ የአግልግሎት ስታንዳርድ አለመዘጋጀትና ቢዘጋጅም በተዘጋጀው ስታንዳርድ መሰረት አገልግሎትን አለመስጠትና የተጠያቂነት ስርዓት አለመኖር ወደ ሪፎም ትግበራ እንዲገባ አስገድዷል፡፡ተገልጋዮች የሚፈልጉትን በአግባቡ ተቀብሎ አለማስተናገድ፣ የአገልግሎት አሰጣጥ ሂደቱ የተንዛዛ መሆኑ እና አገልግሎት አሰጣጡ በሙስናና ብልሹ አሰራር የተበተበ በመሆኑ ነው፡፡ የአንድ ማዕከል አገልግሎት አለመኖር እና አገልግሎት አሰጣጡ በዘመናዊ ቴክኖሎጅ የተደገፈ አለመሆን ተገልጋዮችን ለእንግልት ዳርጓቸዋል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም ሀሰተኛ የትምህርት ማስረጃ፣ የስራ ልምድ፣ የህክምና ማስረጃ እና የመሳሰሉት መኖሩ የመንግስት አገልግሎት አሰጣጥ ሪፎርም አስፈልጎታል፡፡ የተለያዩ ጥናቶች እንደሚያሳዩት በየደረጃው ያለው አመራርና ሰራተኛ ሀሰተኛ የትምህርትና የህክምና ማስረጃ መኖሩ እየታወቀ ለማስተካከል ወደ ስራ አለመግባትና ቢገባም አመራሩ ትኩረት ሰጥቶ ዉሳኔ ለማሳለፍ የቁርጠኝነት ማነስ ይታያል፡፡ በመሆኑም ሃሰተኛ ማስረጃዎች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተበራከቱ መጥተዋል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ የስራ መደብንና የትምህርት ዝግጅትን መሰረት ያደረገ የሙያ ማሻሻያ ስልጠና አለመሰጠቱ በክልሉ ውስጥ ያለው የመንግስት ሰራተኛ በሙያው የሚያኮራና የክብር ምንጭ እየሆነው አይደለም፡፡ ሰራተኛው ይህን ባለመገንዘብ የተቋማቸውን ዓላማና ግብ ለማሳካት ሞራል ያለው፣ ለሙያው የሚጨነቅ ሰራተኛ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሰ በመምጣቱ ሪፎርም ተግባራዊ ማድረግ አስፈላጊ ሆኗል፡፡

የሚደረጉ የቅጥር፣ የደረጃ እድገትና የዝውውር ሁኔቶች የሰራተኛውን እውቀትና ክህሎት በአግባቡ መዝኖ አለማስገባት በስፋት ይስተዋላል፡፡ ብዙ የስራ መደቦችን ትልልቅ ከተሞች በተለይም ዞንና ክልል ያሉ ስራ መደቦች በማህበራዊ ጉዳይ በሚል ከዉድድር ዉጭ በቀጥታ እንዲያዙ ይደረጋሉ፡፡ በዚህ ምክንያት ተቋማት ያላቸዉን የስራ መደብ ዝቅተኛ ተፈላጊ ችሎታ እንዲዘጋጅ ሲያደርጉ ለትምህርት ዝግጅትና የስራ ልምድ የተሰጠዉ ትኩረት ዝቅተኛ በመሆኑ ነው፡፡ ሙያን መሰረት በማድረግ የሚሰጡ ስልጠናዎች በእቅድ የማይመሩ ናቸው፡፡ የክልሉን ተቋማትና የሰዉ ሃይል ማዕከል ያደረገ የለማ ሶፍትዌር እና ደህንነቱ የተጠበቀ ዳታ ሴንተር ባለመገንባቱ ወደ ሪፎርም ትግበራው እንዲገባ አስገድዷል፡፡ በድጅታል ሊሰጡ የሚችሉ አገልግሎቶችን በጥናት ላይ ተመስርቶ ወደ ትግባራ ስላልተገባ የተጓተተ አገልግሎት ተፈጥሯል፡፡ በአንዳንድ ተቋማት አግልገሎትን በድጅታል ለመስጠት የፍላጎትም ሆነ የሰራተኞች አቅም ዝቅተኛ በመሆኑ አግልግሎትን ድጅታል የማድረግ የአሰራር ስርዓት አልተዘረጋም፡፡

የሠራተኛው የሥራ አፈጻጸም ምዘና በግዴለሽነት የሚከናወን በመሆኑ ውጤቱ የጋሸበ እና ከዳይሬክቶሬቱ ወይም ከቡድኑ ምዘና እንዲሁም ከተቋም ምዘና ውጤት ጋር የማይናበብ በመሆኑ የተቋሙ አፈፃፀም ደካማ በሆነበት ለሰራውም ላልሰራውም ተመሳሳይና ከፍተኛ ውጤት የሚሰጥበት ሁኔታዎች በመኖራቸው ነው፡፡



የአማራ ክልል "መሶብ" የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ህንፃ (ባህር ዳር)

ለእዚህ ደግሞ እቅድ ሳይታቀድ ውጤት መስጠት፣ ውጤቱ ምንም ዓይነት ተጠያቂነትም ሆነ ማበረታቻ የማያስገኝና ትርጉም የለሽ መሆኑን በድጋፍና ክትትል ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በአንዳንድ ተቋማት የሠራተኞች የስራ አፈፃፀም ምዘና የእቅድ አፈጻጸም መሰረት አድርጎ የማይሠራና ወጥነት የጎደለው መሆኑ የስራ አፈጻጸም ግምገማ በተጨባጭ መረጃ ላይ ተመስርቶ ከማከናወን አንፃር ጉድለቶች መኖራቸው ነው፡፡

የመንግስት አገልግሎትና አስተዳደር ሪፎርም ዓላማው የታቀዱ ክልላዊ የልማት ግቦችን የሚያሳካና የዜጎችን የአገልግሎት ፍላጎት የሚያረካ የመንግስት አገልግሎትና አስተዳደር ስርዓት ለመፍጠር ያለመ ነዉ፡፡

የመንግስት አገልግሎትና አስተዳደር ሪፎርም መስራት እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡ ምክንያቱም በመንግስት ተቋማት እየተሰጠ ባለው አገልግሎት የተፈጠረውን የመልካም አስተዳዳር ችግር በወቅቱ መፍታት ያስችላል፡፡ እንዲሁም የመንግስት ሰራተኛው በእውቀት፣ በክህሎትና በአስተሳሰብ የተስተካከለ እንዲሆን በማድረግ የልማት ግቦችን ለማሳካት ያስችላል፡፡

የመንግስት ተቋማት ባላቸው የልማት አቅምና የህዝብ ብዛት መሰረት እንዲደራጁ በማድረግ ተቋማትን ደህንነቱ የተጠበቀ፣ ዘላቂነት ያለውና ውጤታማ የሆነ የድጅታላይዜሽን ስርዓት ለመዘርጋት እና በውጤታማነት ሊመራ የሚችል አመራርና ባለሙያ ለመፍጠር አይነተኛ ሚና ስለሚጫወት ነው፡፡

የአሁኑ ሪፎርም ከዚህ በፊት ተግባራዊ ከተደረገው የእኩል ስራ እኩል ክፍያ (JEG) ምዘና በብዙ መልኩ የሚለይ ነው፡፡ ለአብነትም የእኩል ስራ እኩል ክፍያ(JEG) ያሉትን ስራዎች በማጥናትና በመመዘን ለእኩል ስራ እኩል ክፍያ የሚል አሰራር የሚከተል ነበር፡፡ ይህ አዲሱ የመንግስት አገልግሎትና አስተዳደር ሪፎርም ግን ሰባት ምሰሶዎችን በመነሻነት በመውሰድ አጠቃላይ ተቋማዊ ሪፎርም በመስራት መሰረታዊ ለውጥ የሚመጣበት ነው፡፡ እነዚህ ምሰሶዎች ነፃና ገለልተኛ ሲቪል ሰርቪስ ግንባታ፣ አካታችና ብዝሃነት፣ የተቋም አደረጃጀት፣ የሙያ ብቃትን ማሳደግ፣የአገልግሎት ጥራትና ተደራሽነትን ማሳደግ፣ዲጂታል የመረጃ አገልግሎት ጥራት ግንባታ እና ገቢር ነቢብ አመራር ግንባታ ናቸው፡፡



የአማራ ክልል መሶብ የአንድ ማዕከል አገልግሎት የምረቃ ሥነ-ሥርዓት- ባህር ዳር

የሜሪት ስርዓት ተጠብቆ በመንግስት አገልግሎት ዉስጥ ሰራተኛዉ የሚከተለዉ የሃይማኖት፣ የያዘው የፖለቲካ አስተሳሰብ፣ የቋንቋ፣ የባህል ወዘተ ተጽዕኖ ሳያሳድር ነጻና ገለልተኛ ሲቪል ሰርቫንት መፍጠር በመሆኑ ነጻና ገለልተኛ ተቋም ለመፍጠር ፋይዳው ትልቅ ነው::

በተቋም የሚደረገው የመንግስት አገልግሎትና አስተዳዳር ሪፎርም በቅደም ተከተል የሚተገበር ነው:: ምክንያቱም የሚተገብሩ ተቋማት ውጤት እየታየና የአፈጻጸማቸው ተሞክሮ እየተቀመረ ወደ ሌሎቹ የሚሰፋ ነው:: በሌላ መንገድ ድጋፍና ክትትል በማድረግ ተቋማትን በማብቃት ወደ ሪፎርሙ ለማስገባት የሰው ሃይል፣ የቁሳቁስ እና የገንዘብ እጥረት ስለሚገጥም ሁሉንም በአንድ ጊዜ ወደ ሪፎርሙ ማስገባት አልተቻለም::

የመንግስት አገልግሎትና አስተዳደር ሪፎርም የተሳለጡ አገልግሎቶችን ለህብረተሰቡ ለማድረስ በርካታ ጉዳዮችን አካቷል:: ለአብነትም አገልግሎቱን በቴክኖሎጅ በመታገዝና በጥራት ለተገልጋዮች ተደራሽ እንዲሆን ያደርጋል:: የሰራተኞች ብቃት በከፍተኛ ሁኔታ ስለሚያደግ ጥራትና ተገቢነት ያለው አገልግሎት ለተገልጋዮች እንዲደርስ ያስችላል:: ከህብረተሰቡ የአግልግሎት ፍላጎት ጋር የሚጣጣሙ አሰራሮችና አደረጃጀቶች አገልግሎትን ተደራሽ፣ ግልፅ፣ ቀልጣፋ፣ ወጪ ቆጣቢ፣ ችግር ፈቺና ውጤታማ የሆነ አገልግሎት በመስጠት የተገልጋዮችን እርካታን ለማሻሻል ያለመ ነው።

የመንግስት አገልግሎትና አስተዳደር ሪፎርም ለሰብዓዊ ልማት ትልቅ ትኩረት ሰጥቶ የሚሰራ ነዉ:: በመሆኑም የሰራተኞችን አቅም በማሳደግ የመንግስት አገልግሎት ጥራትና ቅልጥፍና በመጨመር የተገልጋዮችን እርካታ ማረጋገጥ ነዉ::

በአገልግሎት አሰጣጥ ላይ የሚቀርቡ ቅሬታዎች እና አቤቱታዎች ለመፍታት የሪፎርም ትግበራው የበለጠ ችግር ፈች ነው:: ደንበኞች ቅሬታቸውን የሚያቀርቡበት የአሰራር ስርዓት ተዘርግቷል:: በአገልግሎት ያገኙትን እርካታ በኤሌክትሮኒክስ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ሃሳባቸውን ይገልጻሉ:: የአገልግሎት ስታንዳርድ ተዘጋጅቶ ስለሚሠጥ የአገልግሎት አሰጣጡም ክትትልና ድጋፍ በወቅቱ ይደረጋል:: ከዚህ ባሻገር የኢንስፔክሽን ስራ ስለሚሰራ አፈጻጸሙ ለክልሉ ምክር ቤት ስለሚቀርብ የበለጠ ግልጸኝነት የሚፈጥር እና ተጠያቂነት ስለሚያመጣ የበለጠ ችግር ፈች ያደርገዋል::

መሶብ ወይም የአንድ ማዕከል አገልግሎት የመንግሥት ተቋማት የሚሰጡትን አገልግሎት በአንድ ቦታ በማሰባሰብ፣ በማደራጀትና ዲጂታላይዝ በማድረግ ሙስና ብልሹ አሰራርን ለማስወገድ ያግዛል::

የአንድ ማዕከል አገልግሎት አሰጣጥ ተደራሽነት፣ ቅልጥፍና፣ ምቾት ቅንጅታዊ አሰራር፣ ተገልጋይ ተኮር እና ግልጽነትና ተጠያቂነት በሚሉ መርሆዎች ላይ በመመስረት ተግባራዊ የሚደረግ ነው:: የመሶብ የአንድ ማዕከል አገልግሎት ተግባራዊ ማድረግ በርካታ ጠቀሜታዎች አሉት:: ለአብነትም ተገልጋዮች ብዙ አገልግሎቶችን በአንድ ቦታ እንዲያገኙ ያስችላል:: የአገልግሎቱን ጥራት፣ ቅልጥፍና እና ውጤታማነት በመጨመር ፈጣን ለውጥ ለማምጣት ያስችላል:: እንዲሁም የአገልግሎት ተደራሽነትን በማሳደግ የተገልጋዮችን እርካታ በመጨመር እና ብልሹ አሰራርን በመከላከል በተገልጋዮችንና በመንግስት መካከል መተማመን ይፈጥራል::

በክልሉ በመጀመሪያው ዙር 10 የክልል ተቋማትና አራት የፌድራል ተቋማት ከ 40 በላይ የተመረጡ አገልግሎቶችን በአንድ ማዕከል ይሰጣሉ:: ከክልል ተቋማት መካከል ሲቪልና ቤተሰብ ምዝገባ አገልግሎት፣ ገቢዎች ቢሮ፣ ትራንስፖርትና ሎጅስትክስ፣ ስራና ስልጠና ቢሮ፣ መሬት ቢሮ፣ ከተማና መሰረተ- ልማት ቢሮ፣ ንግድና ገበያ ልማት ቢሮ፣ ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮ፣ ፍትህ ቢሮና ማእድን ሀብት ልማት ቢሮ ሲሆኑ የፌድራል ተቋማት ኢሜግሬሽና ዜግነት አገልግሎት፣ ኢትዮ ቴሌኮም፣ ኢትዮ ፖስታ፣ ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ናቸው::

በአጠቃላይ የአገልግሎት አሰጣጥን በማሳደግ የአገልግሎት ሽግግር በማድረግ የተገልጋዮችን የጊዜ፣ የገንዘብ እና የጉልበት እንግልትን ይቀንሳል:: አገልግሎቱን በአንድ ቦታ እንዲያገኙ በማድረግ የመንግስት አገልግሎትን በማሳለጥ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት ማምጣት ያስችላል::

በአንድ ማዕከል አገልግሎት ትግበራ የመንግስት አገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ የሚታዩ ችግሮችን በቀላሉ መፍታት ይቻላል፡፡ አገልግሎቱ በቴክኖሎጅ የታገዘ እና ከእጅ ንክኪ ነጻ በመሆኑ ብልሹ አሰራርን ይከላከላል፡፡ በተጨማሪም ተገልጋዮች ከተቋም ተቋም የሚያደርጉትን ምልልስ ከማስቀረቱ ባለፈ አገልግሎትን በአንድ ላይ በጥራትና በፍጥነት እንዲያገኙ ያስችላል፡፡ የአገልግሎት ትስስር(Service Integration) ስለ ሚፈጥር ከተገልጋዩ የሚቀርቡ መረጃዎች አንዴ ብቻ በማቅረብ ለሁሉም አገልግሎቶች ተደራሽ ያደርጋል፡፡

በእርግጥ የአንድ ማዕከል አገልግሎት ለማስጀመር በርካታ ችግሮች ሊያጋጥሙ ይችላሉ ተብሎ ይገመታል፡፡ ለአብነትም የገንዘብ ችግር ሊጋጥም ይችላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በተለይ ዘርፉ አዲስ በመሆኑ በተደራጀ መንገድ ወደ ስራ እሰከሚገባ "አያስፈልግም" የሚል የአመለካካት ችግር ሊያጋጥም ይችላል፡፡ ቢሆንም ግን የአገልግሎቱ ውጤታማነት በጥናት የተረጋገጠ በመሆኑ ከክልል ጀምሮ እስከ ታችኛው የአስተደዳደር እርከን ድረስ የአንድ ማዕከል አገልግሎት እንደ ትልቅ ፕሮጀክት ተይዞ በጀት ለራሱ እየመደቡ በምክር ቤት እያጸደቁ መስራት ያስፈልጋል፡፡ ተከታታይነት ያለው የስልጠና፣ የሚዲያና የኮሙኒኬሽን ስራ ከአመራሩ እስከ ታችኛዉ የህብረተሰብ ክፍል በተደራጀ መንገድ በመስራት የአንድ ማዕከል አገልግሎት አላማና ግቡን በሚገባ ማስረጽ ተገቢ ነው፡፡ የአንድ ማዕከል አገልግሎት ልክ እንደ ሌሎች ትላልቅ ፕሮጀክቶች ከሳምንት እስከ ሳምንት ለ 24 ሰዓታት ያለማቋረጥ በመስራት ወደ ተግባዊ እንቅስቃሴ መግባት ያስፈልጋል፡፡የመንግስት አገልግሎትና አስተዳደር ሪፎርም በውጤታማነት መተግበር ይቻል ዘንድ ከተግባርና ኃላፊነታቸው አንፃር ከፍተኛ ሚና ያላቸው ተቋማቶች አሉ፡፡ በሚኖራቸውም ተግባርና ኃላፊነት መሰረት በርካታ ባለድርሻ አከላትን ያካትታል፡፡



*የመሶብ አንድ ማዕከል አገልግሎት አርማ*

ለአብነትም በየደረጃው ያሉ የሲቪል ሰርቪስና የሰው ሃብት ልማት ተቋማት፣ የትምህርትና ሥልጠና ተቋማት፣ የፌደራል ተቋማት፣ ኢኖቬሽን ቴክኖሎጂ፣ ገንዘብ ቢሮ፣ የስነ-ምግባርና ጸረ-ሙስና ኮሚሽን፣ ፍትህ ቢሮ እና የሲቪክ ማህበራት ናቸው፡፡

ለአብነትም የትምህርትና ስልጠና ተቋማት የሪፎርም ተግባራት በአዳዲስ ሀሳቦች እየጎለበተ እንዲመራ ተከታታይነት ያለው ምርምርና ጥናት ያካሂዳል፡፡ ስለዚህ የዝግጁነት ፣ የሞጁላርና የማሟያ ስልጠና መስጠት እና የብቃትና ምዘና ስራዎችን ለመፈፀም የአጭርና የረዥም ጊዜ ስልጠና እንዲሰጥ ይደረጋል፡፡ የፌደራል ተቋማት ደግሞ በክልሉ የተጀመረውን የሪፎርም ስራ ውጤታማ እንዲሆን በተዋረድ ባሉ ተቋማት የሪፎርም ስራውን በባለቤትነት መምራት፣ ድጋፍና ክትትል ማድረግ እና በበጀት መደገፍ ይጠበቅበታል፡፡

የኢኖቬሽን ቴክኖሎጂ ቢሮ ደግሞ የሪፎርም ስራውን በውጤታማነት ማከናውን የሚያስችል ሲስተም በማልማት ተግባራዊነቱን መከታተል፣ መደገፍና ማስተካከያ የሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች ሲያጋጥሙ የማስተካከል ስራ ለመስራት ያስችላል፡፡

የስነ-ምግባርና ጸረ-ሙስና ኮሚሽን በሪፎርም ትግበራ ወቅት የመንግስት ሠራተኛው መልካም ስብዕናው የተገነባ እንዲሆን ለማስቻል ለዚሁ የሚረዱ የፖሊሲ አቅጣጫዎችን ማመላከት፣ በመንግስት ተቀባይነት እንዲኖረው ማደረግ እና በሲቪል ሰርቪስ ተቋማት እንዲተገበር የድርሻውን ሊወጣ ይገባል ፡፡

የሲቪክ ማኅበራት ደግሞ በሪፎርም ትግበራ ወቅት በየሙያ ማህበራቸው በመንግስት አገልግሎትና አስተዳደር ሪፎርም ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ እና የአስተሳሰብ ማጎልበቻ መርሃ ግብርን በመቅረጽ እና በመተግበር ተገልጋዮቹ የሚረኩባቸው አቅምና ችሎታ ያለው አገልግሎት ሰጭ እንዲኖር ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡

በመጨረሻም አቶ እንዳላማው የመንግስት አገልግልሎት አስተዳደር ተግባራዊ ለማድረግ ባለ ድርሻ አካላት በሁሉም መስከ በተደራጀ መንገድ እገዛ ማድረግ እንደሚጠበቅባቸው በመግለፅ ለሚጠየቁ ጥያቄዎች ተባባሪ በመሆን ምላሽ መስጠት፣እና ባለቤት ሆኖ ስራዎችን መከታተል፣ መገምገምና የማስተካከያ ግብረ- መልስ መስጠት አስፈላጊ መሆኑን በአፅኖት ተናግረዋል፡፡

የ"ሐዲስ" መጽሔት ዝግጅት ክፍልም አቶ እንዳላማውን ለሰጡት መረጃ ከልብ እያመሰገነ የመንግስት አገልግሎትና አስተዳደር ሪፎርም ተግባራዊ ማድረግ የሃገርን እድገት ለማረጋገጥ አገልግሎት ፈላጊው ማህበረሰብ ከአላስፈላጊ የገንዘብ፣ የጊዜ እና የጉልበት እንግልትን ስለሚያስቀር ሁሉም በየደረጃው ያለው የመንግስት አስተዳደርና ማህበረሰቡ ተግባራዊነቱን ለማረጋገጥ በትጋና በንቃት መስራት እንደሚያስፈልግ መረዳት ይኖርባቸዋል በማለት መልዕክቱን ያስተላፋል፡፡

***ሰላም!!***

# የትውልድ ህልም

በደበልጣል መኮንን

የአባይ ወንዝ ውሃ ለዘመናት የሀገራችንን ስቃይና የህዝቦቿን ህልም በሆዱ ይዞ ሲጓዝ ቆይቷል። በሰማይ ጠቀስ ተራራዎቿ ላይ ከሚነሱ ደመናዎች የውሃ እንባውን እያነባ የወደፊቱን የኢትዮጵያ ትውልድ ወደድህነት ሸለቆ እያንከባለለ ይሄድ ነበር። በዚህ ሁኔታ ለረጅም ጊዜ ታላቁን ወንዛችን ሳንጠቀምበት በድህነት ጨለማ ውስጥ እንድንኖር ተገደናል፡፡ የብዙ የአያቶች እና አባቶች ህልም በውሃው አረፋ ላይ ተንሳፍፎ በከንቱ ጠፍቷል። ለሺዎች ዓመታት ኢትዮጵያውያን በአባይ ወንዝ ላይ አልቅሰዋል። ይህ አሳዛኝ የኢትዮጵያ ታሪክ ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ (GERD) እውን

እስከሆነበት ቀን ድረስ ችግሩ ተባብሶ እንደቀጠለ ቆየ።የአባይ ወንዝ ለዘመናት የኢትዮጵያ እና ሌሎች ሃገራት ትልቅ ታሪክ እና የፖለቲካ ውጥረት ማእከል ሆኖ የቆየ ነው። ይህ ታላቅ ወንዝ ከኢትዮጵያ ተራሮች ተነስቶ ሱዳንን እና ግብፅን አቋርጦ ወደ ሜዲተራኒያን ባህር ሲጓዝ የኢትዮጵያ ድርሻ የሆነውን ውሃ ኢትዮጵያ ሳትጠቀምበት በድህነት ውስጥ አሳልፋለች። ዛሬ ግን ያ ታሪክ እና ህልም እውን ሆኖ የታሪክ አሻራ በጋራ ታተመ፡፡

ይህ ፕሮጀክት የአባይ ወንዝን የትውልድ ህልም ወደ እውነታ ለመለወጥ የኢትዮጵያውያን ታታሪነት እና ቁርጠኝነት በተግባር አሳየ፡፡ ይህ ግድብ የኢትዮጵያ ህዝብ ለበርካታ አመታት ሲመኘው የኖረውን የልማት እና የብልጽግና ተምሳሌት በእውን ማሳየት ሲችል የግድቡ ግንባታ ሀገሪቱ በራሷ አቅም እና ገንዘብ የጀመረችው ሲሆን ይህም የኢትዮጵያውያንን የራስ መተማመን እና አንድነትን ያበሰረ ዳግማዊ አድዋ ሆኖ ብስራቱን አሰማ፡፡

"ሐዲስ" መጽሔት በእዚህ ወር እትሟ የግድቡን ታሪክ ፣ የገጠሙትን ፈተናዎች እና የዲፕሎማሲያዊ ውጣ ውረዶችን እና ሌሎች መረጃዎችን ከተለያዩ ገፆች አሰባስባ ያጠናከረችውን መረጃ ለእናንተ ለውድ አንባቢያን እንካችሁ ትላለች መልካም ንባብ፡፡

ለዘመናት በሀገራችን የወንዞች ሀብት ላይ ሲነገር የኖረው ህልም በ21ኛው ክፍለ ዘመን ወደ ትልቅ ፕሮጀክትነት ተለወጠ። ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ የዚህ የረጅም ጊዜ ህልም እውን መሆንን እንዲሁም የአንድነት እና የራስ መተማመን መንፈስ ቁልጭ አድርጎ አሳየ፡፡ ይህ ታላቅ የልማት ምዕራፍ የተጀመረው በወረቀት ላይ በታቀደ ሀሳብ ቢሆንም ከሀሳብነት ወደ ፕሮጀክት ፣ ከፕሮጀክት ወደ ትልቅ ግንባታ እንዲሸጋገር የተደረገው በኢትዮጵያውያን ታታሪነት እና ቁርጠኝነት መሆኑ የተለየ አደረገው።




ታላቁ አባይ "ገነትን ከሚያጠጡት አፍላጋት ምንጮች አንዱ" ሲሆን ከኢትዮጵያ ደጋማ ስፍራዎች ተነስቶ በብዙ ሀገራት አቋርጦ ወደ ሜዲትራኒያን ባህር ሲፈስ ቆይቷል፡፡ የአባይ ወንዝ የኢትዮጵያን ተራሮች ፣ የሱዳንን በረሃዎችና የግብጽን ለም መሬቶች አቋርጦ በሺህ የሚቆጠሩ ዓመታትን ያስቆጠረ ታሪክ ፣ ስልጣኔና የፖለቲካ ውጥረቶችን አሳልፏል።

የአባይ ወንዝ ከኢትዮጵያ መነሻ የሆኑ ሁለት ዋና ዋና ቅርንጫፎች አሉት። አንደኛው ከጣና ሐይቅ የሚነሳውና ሰማያዊ አባይ በመባል የሚታወቀው ነው። ሁለተኛው ቅርንጫፍ ደግሞ ከሩዋንዳ ፣ ቡሩንዲ ፣ ታንዛኒያ እና ዩጋንዳ የሚመነጨው ነጭ አባይ ነው። ነጭ አባይ እና ሰማያዊ አባይ ሱዳን ውስጥ ካርቱም ከተማ አቅራቢያ ተገናኝተው ዋናውን የአባይ ወንዝ ይፈጥራሉ። ከ11 ተፋሰስ ሀገራት ጋር የሚጋራው ይህ ወንዝ የአፍሪካን 10% ያህል ስፋት የሚሸፍን ሲሆን ፣ ለእያንዳንዱ ሀገር ልዩ ልዩ ጠቀሜታ አለው። ለግብጽ እና ሱዳን ከዘመናት በፊት ጀምሮ የስልጣኔ፣ የግብርና እና የውሃ ምንጭ ሆኖ ሲያገለግል የቆየ ሲሆን ለኢትዮጵያ ደግሞ ዋነኛ መነሻ ምንጭ ሆኖ ሳለ ለዘመናት የውሃ ሃብቷን በአግባቡ ለመጠቀም ሳትችል ቆይታለች።

ይህ ፕሮጀክት በወንዙ ላይ የነበረውን "አንድ ማንኪያ ውሃ ሰጥተን አንድ በርሚል ነዳጅ እንቀበላለን" የሚል ጂኦፖለቲካዊ አስተሳሰብ ለውጦ በአገር አቅም እና በሕዝብ ተሳትፎ የውሃ ሃብትን ወደ ልማት ማዋል እንደሚቻል በተግባር ያሳየ ታሪካዊ ምዕራፍ ተከፈተ የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ታሪክ በራሱ አንድ ታላቅ ምዕራፍ ነው። ከዚህም አለፍ ሲል ግድቡ በአንድ መንግስት ብቻ ተጀምሮ ያለቀ ፕሮጀክት አይደለም። የበርካታ መንግስታት ቀጣይነት ያለው ጥረት እና የሕዝብ ልባዊ ተሳትፎ ውጤት እንጅ። ታሪክን በደም ስር ፅፎ ህልም ቀያሪው ትውልድ የአባይ ጉዳይ የጥንት ንጉሶች ራዕይ፣ የዘመናት መሪዎች ምኞት እና የኢትዮጵያ ህዝብ የማይቀለበስ ቁርጠኝነት መገለጫ ነው። ይህ ወንዝ የውሃ ብቻ ሳይሆን፣ የህልውናችን፣ የክብራችንና የወደፊት ተስፋችን ወሳኝ ምሰሶ የትውልድ አደራ የብርሃን ምንጭ ተደርጎ በመሪዎች ልብ ላይ በብሩህ ተፃፈ፡፡

"እኛ አሁን አንችልም፤ ቀጣዩ ትውልድ ግን በራሱ አቅም ይገነባዋል!" በማለት ተስፋንና አደራን በትውልድ ላይ ጣሉ። የዚህን ግድብ ፕላን በወቅቱ በነበረው የ50 ብር መገበያያ ላይ በማሳተም ህልሙን በገንዘብ ምልክት ውስጥ ደብቀው የወደፊቱን ብሩህ ተስፋ በመላው ሕዝብ ልብ ውስጥ ዘሩ።



*"እኛ አሁን አንችልም፤ ቀጣዩ ትውልድ ግን በራሱ አቅም ይገነባዋል!"*

የአባይን ወንዝ የመገደብ ፅኑ ፍላጎት የጀመረው ከሩቅ ዘመናት ቢሆንም ታላቁ መሪ አፄ ኃይለሥላሴ ይህንን ራዕይ ወደ ተግባራዊ ምዕራፍ ለማሸጋገር የመጀመሪያውን ወርቃማ እርምጃ ወሰዱ። በዓለም አቀፍ ደረጃ የተመረጡ ባለሙያዎችን በማሰማራት፣ የግድቡን ምቹነት፣ አዋጭነት፣ ተፈጥሯዊ አቀማመጥና የከርሰ ምድር ጥናት በጥልቀት እንዲያጠኑ አደረጉ። የዚህ ታላቅ ጥናት ፍሬ የሆነው የመጀመሪያው ንድፍ ሲዘጋጅ፣ ስሙም "ወሰን ግድብ (Border Dam)" ተብሎ ተሰየመ። ይህ ስያሜ የወንዛችን ዓለም አቀፍ ትርጉም እና ቦታውን ከወዲሁ አሳየ። ሆኖም ንጉሡ የዘመኑን ነባራዊ ሁኔታ አጢነው፣ የዚያን ጊዜ አገራችን የግንባታውን ሸክም የመሸከም አቅም እንደሌላት ተረዱ። ከውጭም ዕርዳታ ለመጠየቅ ቢሞከር፣ የግብፅን ዲፕሎማሲያዊ ተጽዕኖ በመፍራት ፈቃደኛ የማይሆኑ መሆናቸውን አስተዋሉ። በዚህ ጊዜ የተናገሩት ንግግር የትውልድ ቅብብሎሽ መነሻ ሆነ፡፡




የንጉሡ አደራ በተራው ወደ ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም አመራ። እሳቸውም ለሀገራቸው የውሃ ሃብት ልዩ ትኩረት በመስጠት የመጀመሪያውን የውሃ ተቋም ኢንስቲትዩት አቋቋሙ።



*"አንድ ማንኪያ ውሃ ሰጥተን፣ አንድ በርሜል ነዳጅ እንቀበላለን!"*


ይህ ተቋም የውሃን ጥናትና ልማት በሀገራዊ ዕቅድ ውስጥ ወሳኝ ቦታ እንዲይዝ አደረገ። በዚህ ወቅት የተናገሩት ታሪካዊ ንግግር "አንድ ማንኪያ ውሃ ሰጥተን፣ አንድ በርሜል ነዳጅ እንቀበላለን!" የውሃን ዋጋ በጥልቅ የሚያሳይ ሲሆን ይህ ንግግር ውድ ሀብቶቻችንን በማስተዋል ተጠቅመን ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ለውጥ የምናመጣበትን ወሳኝ መንገድን ጠቆመ። በወቅቱ ምኞቱና ፍላጎቱ ቢኖርም በዚያ ዘመን በሀገሪቱ ላይ የተንሰራፋው የእርስ በእርስ ጦርነት ሁሉንም ትኩረት ወደ ራሱ ስቦታል። በዚህም ምክንያት፣ የአባይ የመገደብ ዕቅድ "ፕሮጀክት ኤክስ" በሚል ሚስጥራዊ ስም በቤተመንግስት መዝገብ ቤት ውስጥ ለዓመታት ተዘግቶ የትውልድ ቁጭትና ህልም ሆኖ ቆየ።



“በመንግሥትና በሕዝብ ተሳትፎ የማይቻል ነገር የለም”

የቅብብሎሽ ችቦው ሦስተኛውን መድረክ ሲደርስ አቶ መለስ ዜናዊ ከሌሎች መሪዎች የተረከቡትን የልማት ጅምር ለማስቀጠል ከፍተኛ ትኩረት ሰጡ። በተለይም በኋለኛው የስልጣን ዘመናቸው የሀገሪቱን የኃይል አቅም ለመጨመር እና ዘላቂ ዕድገት ለማምጣት አባይን የመገደብ ታሪካዊ ዕቅድ ወደ ተግባር ምዕራፍ እንዲሸጋገር አደረጉ። በመጋቢት 24 ቀን 2003 ዓ.ም፣ “በመንግሥትና በሕዝብ ተሳትፎ የማይቻል ነገር የለም” በሚል ጽኑ ህዝባዊ እምነትና ብሄራዊ ቁርጠኝነት የታጀበው የግንባታ ምሰሶ ተጣለ። መጀመሪያ ላይ “የኢትዮጵያ ሚሊኒየም ግድብ” በሚል ስያሜ ተጀመረ። ይህም ግንባታው በአዲስ ተስፋ መጀመሩን ያበሰረ ምልክት ነበር።

ይሁን እንጂ፣ የግድቡ ፋይዳ የአንድ ጊዜ ክብረ በዓል ሳይሆን፣ ለኢትዮጵያ ዘላቂና ዘመን ተሻጋሪ ለውጥ መሆኑን ለማሳየት፣ ስያሜው ወደ “ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ” ተቀየረ። ይህ የስም ለውጥ ከሚስጥራዊነት ወደ ግልጽነት፣ ከአንድ ጊዜያዊ ክስተት ወደ ዘላቂ ህዳሴ መሸጋገሩን አመለከተ። ግድቡ የሀገርን ህልም ታሪክ እና የወደፊት ተስፋ የሚያንፀባርቅ ታላቅ ምሳሌ መሆኑንም አረጋገጠ።



አባይ ወንዝ ከመገደብ በላይ ፣ የኢትዮጵያ የማይበገር የነጻነት፣ የአንድነትና የህዳሴ አርማ ሆነ በታላቅ ድል ከህልም ወደ እውነታ ተቀየረ!



## የጥቁሮች ላብ

ይህ ታላቅ ስራ በቅብብሎሽ የመጣ ፍሬ ነው! ራዕዩን ካነገሡትና አስጀምረው ካለፉት አጼ ኃይለሥላሴ እና ኮሎኔል መንግሥቱ ወደ ተግባር ከመሩትና የመሰረት ድንጋይ ከጣሉት ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ግንባታውን ከተረከቡትና ካስቀጠሉት አቶ ኃይለማርያም ደሳለኝ እስከመጨረሻው ምዕራፍ የደረሰው በዛሬው መሪያችን ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር አብይ አህመድ ሆነ።

ዶ/ር አብይ አህመድ በመጨረሻው ምዕራፍ የነበሩትን ችግሮች አሸንፈው ይህንን ህልም ወደ ፍጻሜ ሲያቀርቡ የተናገሩት ቃል የሁሉንም ትውልድ ጥረት የሚያንፀባርቅ ነው፡- "የግድቡ ስኬት በሁሉም ጥረትና በቅብብሎሽ እውን የሆነ ነው፤ ይህንን ህልም ያለሙ፣ ያሰቡ፣ ያስጀመሩና በዚህ ሥራ ውስጥ የተሳተፉ ጀግኖች በሙሉ እናደንቃለን፤ እናከብራለን፤ የጀመሩትን በመጨረስ ዳግሞ የኢትዮጵያን የትውልድ ቅብብሎሽ በአገር ግንባታ እናረጋግጣለን።" ይህ ታላቅ ግድብ የትውልድ አደራ መፈፀሚያ የዘመናት ቁጭት ወደ ታላቅ ተግባር የተለወጠበት አዲስ ምዕራፍ ነው።

“የእኔ ድርሻ ይሄ ነው!” የሚል የሀገር ፍቅር ቃል ከሁሉም አቅጣጫ ተሰማ። ገበሬው ከአፈሩ፣ ነጋዴው ከኪሱ፣ ሰራተኛው ከደሞዙ፣ ተማሪው ከእርሳሱ፣ እና በውጭ ሀገር የሚኖረው ወገናችን ከሩቅ ምድር ሆኖ ለዚህ ታላቅ ፕሮጀክት እጃቸውን ዘረጉ፡፡ የግድቡ ግንባታ ፋይናንስ በሁለት ዋና ዋና ምንጮች ላይ የተመሰረተ ነበር። እነዚህም የመንግስት በጀት እና የህዝብ ተሳትፎ ናቸው። የመንግስት በጀት ለፕሮጀክቱ ቀጣይነት አስፈላጊውን ገንዘብ ሲያቀርብ፣ የህዝብ ተሳትፎ ደግሞ ለፕሮጀክቱ ባለቤትነት ስሜት እንዲፈጠር ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክቷል። በወቅቱ የተለያዩ ቦንዶቹ በተለያየ ዋጋ ለሁሉም ኢትዮጵያዊያን የሚመች እንዲሆን ተደርጎ ቀርበው ነበር። እነዚህ የቀረቡ ቦንዶች ከገንዘብ ማሰባሰብ ባሻገር ፣ የህዝቡን የባለቤትነት ስሜት ለማጠናከር ትልቅ ሚና ተጫውተዋል። የግድቡን ግንባታ ለመደገፍ የተለያዩ የስፖርት ፕሮጀክት ነው። ፈተናዎችን በዋናነት በሦስት ምድቦች ከፍሎ ማየት ይቻላል፡፡ የፋይናንስ ተግዳሮቶች ፣ የቴክኒክና ጂኦሎጂያዊ ችግሮች እና የፖለቲካና የዲፕሎማሲያዊ ውጥረቶች በወቅቱ የታዩ ችግሮች ነበሩ፡፡

የፋይናንስ የግድቡ ግንባታ በዋናነት ኢትዮጵያ ከዓለም አቀፍ የፋይናንስ ተቋማት ብድር ሳታገኝ ፣ በራሷ ሀብትና ጥረት ለመገንባት በመወሰኗ ተጀምሯል። ይህ ውሳኔ የተወሰነው በውሃ ሀብት ድርሻ ላይ ከሌሎች የታችኛው ተፋሰስ ሀገራት ጋር አለመግባባት ስለነበረ እና የብድር መዳረሻዎች በመዘጋታቸው ነው። የፕሮጀክቱ ጠቅላላ ወጪ እጅግ ከፍተኛ በመሆኑ፣ ሙሉ በሙሉ ከሀገር ውስጥ ሀብት ብቻ መሸፈን ለኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ከፍተኛ ጫና ፈጥሮ ነበር።

የግድቡ ግንባታ ቦታ ያለው የጂኦሎጂያዊ እና የመሬት አቀማመጥ በርካታ ያልተጠበቁ ቴክኒካዊ ችግሮችን ፈጥሮ ነበር። የአፈር እና የድንጋይ ባህሪ የግንባታው ቦታ ለስላሳ ድንጋዮች እና ከፍተኛ የከርሰ ምድር ውሃ የያዘ በመሆኑ ለፕሮጀክቱ ተጨማሪ ጥናትና የሥራ ጊዜ አስፈልጎ ነበር። እንዲሁም በኢትዮጵያ ምዕራባዊ ጫፍ ሩቅ ቦታ ላይ የሚገኝ በመሆኑ የመሠረተ ልማት እምብዛም ባለመሟላቱ ለግንባታ የሚያስፈልጉ ከባድ ማሽነሪዎችንና ጥሬ ዕቃዎችን ማጓጓዝ አስቸጋሪና ውድ ነበር።





*በታላቁ አባይ ግድብ ከተሳተፉት ማሽነሪዎች ጥቂቶቹ*

ከታችኛው ተፋሰስ አገሮች በተለይም ከግብጽ እና ሱዳን ጋር የውሃ አጠቃቀምን በተመለከተ ዲፕሎማሲያዊ ውዝግቦችንና ውጥረቶችን ፈጥሮ ነበር። ግብጽ ግድቡ "ታሪካዊ የውኃ ድርሻየ ይቀንስብኛል" የሚል ስጋት የነበራት ሲሆን ኢትዮጵያ ደግሞ "በራስ አቅም የተፈጥሮ ሀብቴን መጠቀም የሉዓላዊነቴ መገለጫ ነው" የሚል ጠንካራ አቋም ነበራት። የግብጽ መንግስት በዓለም አቀፍ መድረኮች እና እንደ አረብ ሊግ ባሉ ተቋማት አማካኝነት በኢትዮጵያ ላይ ጫና ለማሳደር ሞክሯል፡፡ ይሁን እንጅ ወታደራዊ ዛቻውንና የፖለቲካ ጫናን በዲፕሎማሲያዊ ጥበብ ተቋቁማለች። የግድቡን የጋራ ጥቅሞች ፣ ለምሳሌ የጎርፍ መከላከል ፣ የአፈር ለምነት ቁጥጥር እና የክልል ትብብርን በመጥቀስ ፣ ውጥረቱን ከግጭት ወደ ትብብር ለማሸጋገር ጥረት አድርጋለች። የአፍሪካ ጉዳዮች በአፍሪካ ህብረት መድረክ ውስጥ መፈታት እንዳለባቸው አቋም በመውሰድ የውጭ ጣልቃ ገብነትንም ተቋቁማለች።

ከዘመናት በፊት የአባይ ወንዝን ኃይል ለመጠቀም የታቀደው የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ (GERD) ፕሮጀክት አሁን እውን ሆኗል። ይህ ታሪካዊ ፕሮጀክት የኢትዮጵያን የኢኮኖሚ፣ ማህበራዊ እና የፖለቲካዊ ገጽታዎች በእጅጉ ሊለውጥ የሚችል ታላቅ የልማት ምሰሶነቱን አሳየ። የህዳሴው ግድብ የኢትዮጵያን ብልጽግና ጉዞ ለማፋጠን ከመንገድ ጠራጊነት በላይ ፣ ለሀገሪቱ ታላቅነት ማሳያ የሆነ ትልቅ ምልክትም ተደረገ። የሀገር ኢኮኖሚ ዋና የደም ስር የሆነው የኤሌክትሪክ ኃይል ከረጅም ጊዜ በፊት የነበረው የኃይል እጥረት የኢትዮጵያን ልማት ጎዳና ከሚያደናቅፉ ነገሮች አንዱ ነበር። አሁን ግን ይህ ታሪክ ተቀየረ። የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ በዓመት እስከ 15,000 ጊጋዋት ሰዓት (GWh) የኤሌክትሪክ ኃይል የማመንጨት አቅም ያለው ሲሆን ይህ የኃይል መጠን ለሀገሪቱ የኢንዱስትሪ መስፋፋት ዋነኛ መሠረት የሚጥል ነው።

በቂ እና አስተማማኝ የኃይል አቅርቦት መኖር የኢንዱስትሪዎችን እና የፋብሪካዎችን ቁጥር እንዲጨምር ያደርጋል። ይህ ደግሞ አዳዲስ የሥራ ዕድሎችን በመፍጠር ፣ የምርት አቅምን መጨመርና የሀገር ውስጥ ገቢን በማሳደግ የኢኮኖሚ እድገቱን ያፋጥነዋል። ከዚህም በተጨማሪ፣ ንፁህ እና ታዳሽ የኃይል ምንጭ በመሆኑ የአካባቢን ተግዳሮቶች ለመቋቋም ትልቅ አስተዋጽኦ ያደርጋል። በውሃ ኃይል የሚመነጨው ይህ ኤሌክትሪክ የካርቦን ዳይኦክሳይድ ልቀትን ስለሚቀንስ ኢትዮጵያ የአየር ንብረት ለውጥን ለመቋቋም ለምትደረገው ዓለም አቀፍ ትግል ያላትን ቁርጠኝነት ያሳያል። ከኃይል ምንጭነት ባሻገር የግብርናው ዘርፍ የጀርባ አጥንት በመሆን የሀገሪቱን ኢኮኖሚ እንደሚጠግን እምነት ተጥሎበታል፡፡ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ዋነኛ መሠረት የሆነው የግብርናው ዘርፍ ከህዳሴው ግድብ ዋነኛ ተጠቃሚ ነው። ግድቡ በሺዎች የሚቆጠሩ ሄክታር መሬቶችን ለማልማት የሚያስችል የውሃ ክምችት ይፈጥራል። ይህ ደግሞ በዝናብ ላይ ብቻ ጥገኛ የነበረውን የግብርና ስራ በማስቀረት አርሶ አደሮች አመቱን ሙሉ ምርት እንዲያመርቱ ያስችላቸዋል። የመስኖ እርሻ መስፋፋት የግብርና ምርቶችን መጠንና ጥራት ከፍ ያደርጋል። ይህም የሀገሪቱን የምግብ ፍላጎት ለማሟላትና የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ ወሳኝ ሚና ይጫወታል።

የቱሪዝም እና የኢንቨስትመንት መስህብ በመሳብ የህዳሴው ግድብ የተፈጥሮ ውበትን ከዘመናዊ የቴክኖሎጂ ስራ ጋር በማዋሃድ ለቱሪዝም ዘርፉ አዲስ ምዕራፍ ከፍቷል። ግዙፉ የግድብ ግድግዳ እና የተፈጠረው ሰፊ ሐይቅ በአካባቢው ልዩ የሆነ የመልክዓ ምድር ገጽታ ፈጥረዋል። ይህም የአገር ውስጥ እና የውጭ ቱሪስቶችን በመሳብ ለሆቴሎች ፣ ለምግብ ቤቶች እና ለሌሎች የአገልግሎት መስጫ ተቋማት እድገት ትልቅ አስተዋጽኦ የሚያደርግ ነው። በተጨማሪም የተረጋጋ የኃይል አቅርቦት መኖር የውጭ ባለሃብቶች በኢትዮጵያ ኢንቨስት እንዲያደርጉ ያበረታታል።




*ጠ/ሚ ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ጳጉሜን 4/2017 ዓ.ም ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብን ምርቃት*

ይህ ደግሞ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን፣ እውቀትን እና የውጭ ምንዛሪ ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገባ ያግዛል።

የውጭ ምንዛሪ ቁጠባ እና ገቢ ምንጭ የታላቁ ህዳሴ ግድብ ዋነኛ ጥቅሞች አንዱ የውጭ ምንዛሪ መቆጠብ እና ማስገኘት ነው። ከዚህ በፊት ኢትዮጵያ የነዳጅ ነዳጅ በመግዛት የኤሌክትሪክ ኃይል ለማመንጨት ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ታወጣ ነበር። የግድቡ ግንባታ ይህን ውድ ወጪ በመቀነስ የሀገሪቱን የውጭ ምንዛሪ ይቆጥባል። በሌላ በኩል ኢትዮጵያ ከግድቡ በሚገኘው የኤሌክትሪክ ኃይል በመጠቀም ለጎረቤት ሀገራት እንደ ሱዳን ፣ ኬንያ እና ጅቡቲ በመሸጥ የውጭ ምንዛሪ ገቢ ታገኛለች።

ይህ ታላቅ ህልም የዘመናት ቁጭት መካሻ፣ በፈተናዎች ሁሉ ተቋቁሞ የመጨረሻውን የድል ፅዋ ተጎናጽፏል። የህዳሴው ድል ዳግማዊ የአድዋ ድላችን ፣ የብሔራዊ አንድነታችን ዓርማ በመሆኑ፣ ለእኛ አልፎ ለመላው ጥቁር ሕዝብና ለዓለም ታላቅ ማሳያ ያውን አበሰረ።

ይህ ግዙፍ ግንባታ የአፍሪካ አንደኛ እና በዓለም 10ኛ በመሆን፣ አምስት ሺህ አንድ መቶ ሃምሳ (5,150) ሜጋ ዋት የኤሌክትሪክ ኃይል የማመንጨት አቅም ያለው ነው።

74 ቢሊዮን ኪዩቢክ ሜትር ውሃ የመያዝ አቅሙ (ሁለት የጣና ሐይቅ ያህል) ሲሆን፣ የተፈጠረው ሐይቅም "ንጋት" በሚል ስያሜ ከ80 በላይ ደሴቶች ተፈጥረውበታል። ይህ ኃይል 60 ሚሊዮን ለሚሆን ሕዝብ የኤሌክትሪክ አገልግሎት የሚያስገኝ ሲሆን፣ በ2030 ዓ/ም 10 ሚሊዮን ኢትዮጵያንን ከድህነት ለማላቀቅ ቁልፍ ተስፋ ተጥሎበታል። የግድቡ ርዝመት 1 ነጥብ 8 ኪሎ ሜትር ሲሆን፣ ቁመቱም 145 ሜትር (ከ40-45 ፎቅ ከፍታ) ያለው ግዙፍ ኮንክሪት ነው። በአባይ ወንዝ ላይ 14 ዓመታትን በወሰደ የጀግንነት ጉዞ የተገነባው ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ፣ ጳግሜ 4 ቀን 2017 ዓ/ም በጠቅላይ ሚኒስተር ዶ/ር ዐብይ አህመድ እና በተጋባዥ ዓለም አቀፍ መሪዎችና ኃላፊዎች በተገኙበት በደማቅ ሥነ-ሥርዓት ተመርቋል።

በአጠቃላይ ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ከአንድ የሲሚንቶና የብረት ግንብ የዘለለ፣ የሀገር ልብ ምት፣ የብሔራዊ ኩራትና የሉዓላዊነት አርማ ሆኖ የኢትዮጵያን ታሪክ ዳግም የጻፈ ዘመን ተሻጋሪ ፕሮጀክት ነው። የግድቡ ግንባታ የሀገር ውስጥ የገንዘብ አቅምን በማሰባሰብና የቴክኒክ ክህሎትን በማጎልበት የህዝብን የጋራ ዓላማ በማጠናከር የልማት ራዕይን ወደር የለሽ በሆነ መንገድ አጎናጽፎናል።

በኢትዮጵያ ምድር የዘመቻ መሪ ቃል ሆኖ የተሰማው "በኅብረት ችለናል" የሚለው ቃል፣ የግድቡን ግንባታ ከገንዘብ ማሰባሰብ ዘመቻነት ወደማይናወጥ ብሔራዊ የአንድነትና የትጋት ቃል ኪዳን ከፍ አድርጎታል። እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ለፕሮጀክቱ ድል ያለውን የማይተካ ድርሻ እንዲሰማው በማድረግ፣ በጋራ መንፈስ ለስኬቱ አስተዋጽኦ አድርጓል። ይህ ደግሞ ግድቡን ከኃይል ማመንጫነት ወደ ዘላቂ የነፃነትና የኩራት ምንጭ ከፍ አድርጎታል። ከምንም በላይ የህዳሴው ግድብ ምህንድስናዊ ገድል የኢትዮጵያን ብልህነት ፣ ዲፕሎማሲያዊ ብስለትና የቴክኒክ አቅምን አጉልቶ በማሳየት ደማቅ ምስክር ነው። በተለያዩ የውጭ ጫናዎችና ተግዳሮቶች ውስጥ ሳይናወጽ ወደ ፍጻሜው መድረሱ፣ ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ መድረክ ላይ ያላትን አቋም እና ራዕይ በማያወላውል መልኩ አጠናክሯል። ፕሮጀክቱ ለቀጣይ ትልልቅ የልማት ምዕራፎች ታላቅ ትምህርት ሰጥቷል፡፡ በተለይም የእውቀት ሽግግር ፣ የፋይናንስ አስተዳደር ግልጽነት እና የአካባቢና ማህበራዊ ጥበቃ አስፈላጊነትን አሳይቷል። ይህ ትውልድ በራሱ አቅም ታሪክ መፍጠር እንደሚችል በግልጽ አሳይቷል፡፡ ኢትዮጵያ የአዲስ አፍሪካ ምዕተ ዓመት ሞተር መሆን እንደምትችል የሚያሳይ ደማቅ የትውልድ ማስረጃ ነው።

በመሆኑም ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ የትውልዶች ህልም በልዩ ጀግንነት እውን የሆነበት ዘመን ተሻጋሪ ሰነድ ነው ብሎ በሙሉ ልብ መናገር ይቻላል፡፡ ይህ ግድብ የኢትዮጵያና የአፍሪካ የጋራ ዕድገትና ትብብር ምልክት በመሆን ለቀጣይ ትውልዶች የኩራት አደራ ነው። በአባይ ላይ የተገነባው ይህ የኩራት ምሰሶ፣ ለሌሎች ሀገራዊ ፕሮጀክቶች ሁሉ የመንፈስ ምንጭ ሆኖ የሀገሪቱን የልማት ጉዞ በጽናት እንዲቀጥል እናሳስባለን ሰላም!

የመረጃ ምንጭ:-

*በታላቁ ህዳሴ ማስ/ፕ/ጽቤት አስተባባሪነት የተዘጋጀ ልዩ እትም ቁጥር II (አዲስ አበባ) ፣ EBC ፣ FANA፣ እና NBC TV ላይ ለአምዱ በሚመጥን መልኩ ተሻሽሎ የተወሰደ ፡፡*

# ዋጋው የላቀ. . .

በህያው ተስፋዬ



የሰላም ጉባኤ በአማራ ክልል

“ሰላም ” የሚለው የአማርኛ ቃል ከጦርነትና ከአመፅ ነፃ መሆን ከሚለው በላይ ትርጉም እንዳለው አንዳንድ መዛግብት ይገልፃሉ ። “ ሰላም “ ለሰው ልጆች ከፈጣሪ የተሰጠ ስጦታና ውድ ጸጋ ነው። በክርስትና እምነት ተከታዮች ዋና በሆነው መጽሐፍ ቅዱስም «እግዚአብሔር ሰላም ነው» ይላልና።አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ የሰላምን ፍቺ “ ፍጹም፣ ጤና፣ ዕረፍት፣ ዕርቅ፣ ፍቅር፣ አንድነት፣ ደኅንነት፣ ተድላ፣ ደስታ፣ ሰላምታ፣ የቡራኬ የምርቃት ቃል፣ ሰው ሲገናኝና ሲለያይ የሚለው እንዲሁም የሚናገረው ወይም የሚጽፈው ነው ” በማለት ይገልጹታል። በርግጥም ሰላም የሁሉ ነገር ዋስትና ነው። ሰርቶ የመለወጥ፣ ወልዶ የማሳደግ፣ ወጥቶ የመግባት፣ ዘርቶ የማፍራት በአጠቃላይ በሰው ልጆች የእለት ተእለት ተግባር ውስጥ ከምንተነፍሰው አየር ያልተናነሰ ዋጋ አለው። ሰላም ከሌለ ነገ የለም። ስለ ነገ ማሰብም ማቀድም የሚቻለው በሰላም ውስጥ ነው። የሰላምን ምንነት ለመረዳት ሰላም የግጭትና ጦርነት አለመኖር፣ በሰዎች መካከል የመቀራረብ፣ የመግባባት፣ ግጭቶችን በንግግር የመፍታትና የመምራት ሁኔታንም ይመለከታል።

ስለዚህ ሰዎች ከራሳቸውና ከአካባቢያቸው ጋር ሰላም ኖሯቸው ለጋራ እድገትና አብሮ መኖር አስተዋጽኦ ካደረጉ ሰላም አለ ማለት ነው። በእያንዳንዱ ሕብረተሰብ ዘንድ ውስጣዊና ውጫዊ ስምምነት ካለ ሰላም አለ ማለት ይቻላል። ስለዚህ ሰላም ከፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ኑሮ ባሻገር ሰዎች ከሰዎች፣ ከተፈጥሮና ከአካባቢ ጋር ያላቸውን ግንኙነት ስለሚመለከት ሰላም ሁሉን አቀፍ ይዘት አለው። በተለይ የሰላምን ጥቅም ካለመረዳት፣ በሥጋዊ አስተሳሰብ መጠመድ፣ ነገን መርሳት፣ ፍቅር አልባነት፣ ጊዜያዊ ጥቅም፣ ድህነት፣ ሥራ ፈትነት እና መሰል ተግባራት ሲበዙ እንደሆነ ይታወቃል። በዚህም ምክንያት በማኅበረሰብ ውስጥ ባሉ አንዳንዴም ተቃራኒ በሆኑ የፖለቲካ አስተሳሰቦች ያልተጣጣሙ ፍላጎቶች የተነሣ የፖለቲካ ትግል ይፈጠራል።

በዚህ ዓይነት የተፈጠረው የፖለቲካ ትግል የሚካሄደው ደግሞ አልፎ አልፎ ሕጋዊና ሞራላዊ በሆነ መልኩ ሲሆን አንዳንድ ጊዜ ደግሞ የማኅበረሰቡን ባሕል፣ ሕግ፣ እምነትና ግብረ ገብነትን በተቃረነ መንገድ ይሆናል። ቢሆንም ግን ከግጭት የሚያተርፍ ስለሌለ ብቻ ሳይሆን ሰላም ከምንም በላይ በመሆኑ ለሰላም ፍሊጋ የማይጓዙት ርቀት የማይወጡት ዳገት አይኖርም። የተረጋጋ ሰላም እንዲፈጠር ትኩረት ሰጥቶ መሥራት እና የሰላም አደፍራሽ ሁኔታዎችን ቀድሞ መከላከል እንደሚያስፈልግ ምንም ጥርጥር የለውም።

የሀገራችን ኢትዮጵያን ታሪክ ስናይ ደግሞ ግጭቶች ሌላ ግጭት እየወለዱ የግጭት አዙሪት ውስጥ ተነክረን ያለፍንባቸው ሰላም አልባ ዘመናት በርካታ ናቸው። ድሃ አገራት በድህነታቸው እንዲቀጥሉ ካደረጋቸው የልማት ወጥመድ መካከል አንዱ የግጭት ወጥመድ እንደሆነ ታላላቅ ምሁራን ይናገራሉ። በተለይ የእርስ በርስ ግጭት አንድን አገር ከፍተኛ የኢኮኖሚ ውድመት ውስጥ እንደሚከትና የእርስ

በርስ ግጭቱ እየተራዘመ በመጣ ቁጥር ደግሞ ከግጭቱ የሚያተርፉ አካላት እየበረከቱ ስለሚመጡ ለቀጣዩ ግጭት መፈጠር በር ከፋች ይሆናል ይላሉ፡፡

በተጨባጭ እንደታየውም ለዘመናት ሲዘሩ የቆዩ የጥላቻና የመከፋፈል ዘሮች ፍሬ አፍርተው ሕብረተሰባችንን ያስተሳሰሩት ክሮች እየላሉና እየተበጣጠሱ መጥተው መንገራገጭ ደረጃ ላይ ደርሰናል፡፡ በመሆኑም ከዚህ ችግር ለመውጣት “ምክንያታዊ” ሆነን ሰላምንና የሰላምን መንገድ መውሰድ አማራጭ የሌለው መፍትሄ መሆኑን ያሳየናል፡፡

የቀድሞ የሰላም ሚንስትር የተከበሩ ብናልፍ አንዷለም ባንድ ወቅት እንዲህ ብለው ነበር፡፡ “ምርጫችን ሰላም ከሆነ ሰላም እንሆናለን፣ ምርጫችን ግጭት ከሆነ ሰላማችንን እናጣለን ስለዚህ ምርጫችንን ማስተካከል ይኖርብናል ” በማለት ተናግረዋል።

በዚህ ረገድ መንግሥት ፍትሃዊነትን በማስፈን፣ ዲሞክራሲን በማስረፅ፣ የፍትሕ ተቋማትንም ገለልተኛ እንዲሆኑ በማድረግ ለዜጎች ለሰላም ትኩረት መስጠቱ እንደተጠበቀ ሆኖ የሃይማኖት ተቋማት፣ የአገር ሽማግሌዎችና መሰል ተቋማት ከፍተኛ ሚና ይጠበቅባቸዋል፡፡ እንደሚታወቀው የኃይማኖት አባቶች ይቅርታንና አንድነትን ስለሚሰብኩ በተከታዮቻቸው ዘንድ ከፍተኛ ተቀባይነት አላቸው፡፡

አባቶች በየቤተ ዕምነታቸው ለልጆቻቸው ስለሰላም በመስበክ ግጭት እንዳይፈጠር ቢፈጠር ደግሞ በእርቅ የመፍታት ኃይማኖታዊ ተልዕኮን የማስረጽ ኃላፊነት አለባቸው፡፡

ዜጎች ኃይማኖታቸውን በነፃነት ማራመድ የሚችሉት ሰላም ሲኖር በመሆኑ ሀገራችን ውስጥ ያሉ ሁሉም ኃይማኖቶች በ “ሰላም" አስፈላጊነት ብቻ ሳይሆን ለሰላም ምልክት በመሆን በተግባር የተገለጠ አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ የዘወትር ስራቸው ሊሆን ይገባል፡፡



**መልዓከ ሰላም ለዓለም ጌታሁን**
የባህር ዳር ርዕሰ ከተማ ወረዳ ቤተ ክህነት ጽ/ቤት ሥራ አስኪያጅ እና የባሕር ዳር ከተማ የኃይማኖት ተቋማት ጉባኤ ሰብሳቢ

የአማራ ክልል አሁናዊ ሁኔታን ስናይ ደግሞ በተረጋጋ ሰላም ውስጥ አለመሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ካለፉት ጥቂት ዓመታት ጀምሮ አለመግባባቶችን ያለ ሰብአዊና ቁሳዊ ውድመት በመመካከር ማስተካከል የሚቻልበትን ዕድል ባለመጠቀም የጦርነት ዘመቻ በከፈቱ ጥቂት የክልሉ ተወላጆች ምክንያት ህዝቡ የመጀመሪያ ደረጃ ተጠቂ ሆኗል፡፡ ሆኖም ግን በዕርስ በርስ መገዳደል ማንንም አሸናፊና ተሸናፊ ማድረግ ስለማይቻል የክልሉ መንግስት በሰላማዊ የትግል አማራጮች ዙሪያ መነጋገር እንዲቻል የሰላም በሮችን ክፍት ለማድረግ ጥረት አድርጓል፡፡ በርግጥም ደግሞ ይህን አማራጭ በትክክል ልንጠቀምበት የሚገባና የህዝቡን ጉዳት ማስወገድ የግድ መሆኑን ያመኑና ከጥፋት መንገዳቸው ተመልሰው ወደ ሰላማዊ ኑሯቸው የተመለሱ ታጣቂዎች ቁጥር ከፍተኛ ነው፡፡

ነገር ግን አሁንም ቢሆን ህዝቡ ከስጋት፣ ከብዝበዛ፣ ከእገታና ከሞት የተላቀቀ ባለመሆኑ ሰላማዊ እንቅስቃሴው በሚፈለገው መጠን አለመተግበሩ ይታወቃል፡፡ ይህም ብቻ ሳይሆን « ጅብ በቀደደው ...» እንዲሉ በክልሉ ላይ እየተካሔደ ባለው ጦርነት ምክንያት በተከሰተው የፀጥታ መደፍረስ ሌሎች የከተማ እና የገጠር ውስጥ እገታ፣ ዝርፊያ፣ ስርቆትና ረብሻ የመሳሰሉ የፀጥታ ችግሮች የህዝቡን የዕለት ከዕለት እንቅስቃሴዎች እያወኩት ይገኛሉ፡፡

ይሁን እንጂ የተበላሹ ነገሮች ሁሌም መስመራቸውን እንደለቀቁ ይቀጥላሉ ማለት አይደለም፡፡ መስተካከል በሚገባቸው አግባብ እንዲስተካከሉ መንግስት ሁሉንም አማራጮች እየተከተለ ይገኛል፡፡

አንደኛው የመፍትሔ መንገድ ደግሞ ሁሉም የዕምነት ተቋማት ለሰላም ያላቸውን ዋጋ ተግባራዊ በማድረግ ተባባሪ እንዲሆኑ የማድረግ ሥራ ነው፡፡ ለዚህም በክልል ደረጃ የኃይማኖት ተቋማት ጉባኤ ተቋቁሞ በርካታ ስራዎችን እየሠራ ይገኛል፡፡

የዝግጅት ክፍሉም ከባህርዳር ከተማ የኃይማኖት ተቋማት ጉባኤ አመራሮች ጋር ያደረግነውን ቆይታ እንደሚከተለው አቅርበናልና ተከታተሉት፡፡

በቅድሚያ በህብረቱ ዙሪያ ያለውን መረጃ ያጋሩን መልዐከ ሰላም ለዓለም ጌታሁን ይባላሉ፡፡ የባሕር ዳር ከተማ የኃይማኖት ተቋማት ጉባኤ ሰብሳቢ ናቸው፡፡ እርሳቸው የሚመሩት ይህ ጉባኤ ከ2005 ዓ.ም ጀምሮ ወደ ስራ እንደገባ እና የተቋቋመበት ዓላማም በመከባበር፣ በመቻቻል እና በፍቅር ላይ የተመሠረተው የኢትዮጵያዊነት እሴቶች እንዳይጠፉ ብሎም ተጠናክረው እንዲቀጥሉና ሰላማዊት ሀገር እንድትኖረን የእምነት ተቋማት የበኩላቸውን ድርሻ እንዲወጡ በማሰብ የተቋቋመ ነው፡፡

ባሕር ዳር ከተማ ውስጥ የሚንቀሳቀሱ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን፣ እስልምና እና የወንጌል አማኞችን ጨምሮ ሰባት የዕምነት ተቋማት የጉባኤው አባላት ሲሆኑ ፤ ሁሉም የኃይማኖታቸውን ልዩነት አክብረውና በመካከላቸውም ግጭት እንዳይፈጠር በየአስተምህሯቸው እንደሚሰበኩ ገልፀውልናል፡፡

" እንኳን ለሰው ልጅ ህይወት ላለው ፍጥረት ሁሉ ሰላም ስለሚያስፈልገው በየ እምነቶቻችን ሰላምን አጥብቀን እንድናስተምር እንገደዳለን፡፡ ምክንያቱም እረኛ እንደሚያስፈልገው የእንስሳት መንጋ የቤተ እምነቶቻችን ተከታዮቻችንም ፈጣሪ በሚያዘን ልክ በመልካም ስብዕና የታነጹ ሰዎች እንዲሆኑ መስራት ግድ ይላል፡፡ ህዝቡም እረኛው ወደሚፈልገው እንደሚሠማራ መንጋ የእምነት አባቶቹ የሚሉትን ይሰማል፡፡

በርግጥ ይህ በሁሉም ተከታዮቻችን የሚታይ መገለጫ ባይሆንም በአንዳንዶች ዘንድ አልፎ አልፎ የሚታዩ ችግሮች አሉ፡፡ ለዚህ ነው እኛ ያስፈለግነው፡፡ ሰዎች በእምነታቸው እያደጉ መጥተው በእጅጉ የተሸለ ሰላማዊ እንቅስቃሴ እንዲኖራቸው ሁሌም እንሠራለን፡፡ በተለይ ደግሞ አሁን በአማራ ክልል ከተፈጠረው የፀጥታ ችግር አኳያ ቤተ እምነቶች የበለጠ ስራ እንደሚጠበቅባቸው ይታወቃል፡፡

ከዚህ አኳያ የከተማው ቤተ እምነቶች ጉባኤ በክልሉ ካለው ችግር ስፋት አንፃር በሚጠበቅበት ልክ ሰርቷል ባይባልም በመንግስትና በተፋላሚው ኃይል መካከል መቀራረብ እንዲኖርና ችግሮቻቸውን መፍታት እንዲችሉ የቻልነውን ያክል ጥረት አድርገናል፡፡ ይህ እንዲሆን ግን እውነት አንድ እንደሆነች ሁሉ ሁለቱ ኃይሎች ወደ ሰላም ለመምጣት ሊፈጽሟቸው የገቧቸውን ቃሎች ያለ ምንም መሸራረፍ መፈፀም እንድንችል የበኩላችንን ጠረት እናደርጋለን፡፡

የእምነታችን ተከታዮቻችንም መልካም ማድረግ ሁሌም የተፈቀደ ስለሆነ በየአብያተ ክርስቲያናት የሚሰበከውን መንፈሳዊ ስብከት በተግባር ማሳየት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ከዚህ ውስጥ ደግሞ አንዱ የሰላም ጉዳይ ነው፡፡ ሰላምን ሁሌም ከሌሎች ሰዎች ብቻ መጠበቅ ሞኝነት ነው፤ ራሳችንም ሰላማዊ መሆንና ለሰላም ተባባሪዎች መሆን ያስፈልጋል ፡፡



**መጋቢ ደሳለኝ አባተ**
የባሕር ዳር ከተማ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ህብረት ዋና ፀሐፊ እና የባህር ዳር ከተማ የኃይማኖት ተቋማት ጉባኤ ፀሐፊ

በመንግስት በኩልም በየጊዜው ከህዝቡ ጋር ውይይት በማድረግ በሰላም ዙሪያ በጋራ ለመስራት እያደረገ ያለው ጥረት ጥሩ ነው፡፡ ሆኖም ግን በክልሉ ላይ የተፈጠረውን የሰላም መደፍረስ ማስተካከል ካስፈለገ ከተፋላሚ ኃይሎችም ጋር ለመወያየት የበለጠ ጥረት ማድረግ ይገባዋል፡፡ በተጨማሪም ራሱ ካቋቋመን ከክልሉ የኃይማኖት ተቋማት ጉባኤ ጋር የተቀራረበ ስራ መስራት ይጠበቅበታል" ብለዋል፡፡

ሌላኛው እንግዳችን መጋቢ ደሳለኝ አባተ ይባላሉ፡፡ በአማራ ክልል የባህር ዳር ከተማ የኃይማኖት ተቋማት ጉባኤ ፀሐፊ ናቸው፡፡ እርሳቸውም በበኩላቸው ጉባኤው የተቋቋመበት ዓላማ መላዕከ ሰላም ከገለፁት በተጨማሪ ሁላችንም በየቤተ እምነቶቻችን የፖለቲካ አንድምታ ያለው ሀሳብ እንዳይራመድ ወይም ቤተ እምነቶቻችን ከፖለቲካ አስተሳሰብ ውጭ እንዲሆኑ ማድረግ ነው፡፡ ከዚያ ባሻገር በሰላም ጉዳይ የየቤተ እምነቶች ዋና አጀንዳ በመሆኑ ሁሉም የሰላም ሰባኪዎች ናቸው ማለት ይቻላል፡፡ ማለትም ስለ ሰላም መስበክም ሆነ ማስተማር ግዴታ እንጂ ውዴታ አይደለም፡፡

በተለይ ከግጭት በፊት ሰዎች በሰላም ተከባብረውና ተቻችለው እንዲሁም ተፋቅረው እንዲኖሩ የሚችሉበትን የፈጣሪ መንገዶች እናስተምራለን፡፡ ለምሳሌ በመጽሐፍ ቅዱስ " ሻካራ ቃል ጠብን ያነሳሳል " እንደሚል ከጠብ በፊት ሰዎችን የሚያሳዝኑ፣ የሚያስቆጡ ወይም ለጠብ የሚያነሳሱ ነገሮች እንዳይፈጠሩ ከንግግር ጀምሮ መቆጠብ እንዲቻል እናስተምራለን፡፡ ማለትም ሰዎች ከጥፋት ይልቅ መልካምነትን፣ ከጊዜያዊነት ይልቅ ዘላቂ ሰላምን እንዲመርጡ ሁሌም እናስተምራለን፡፡ በተለይ ደግሞ በአፍላ የወጣትነት የእድሜ ክልል ያሉ ወጣት ልጆቻችን አንድን ነገር ማድረግ ስለቻሉ ብቻ ማድረግ እንደሌለባቸው እና አንድን ድርጊት ከመፈፀማቸው በፊት በማስተዋል ጥቅምና ጉዳቱን መዝነው እንዲያደርጉት እናስተምራቸዋለን፡፡

ለዚህ ደግሞ ከየ እምነት ተቋሞቻችን ባሻገር በሰፊው ማህበረሰብ ዘንድ ተደራሽ እንዲሆን የሚዲያ አማራጮችን በመጠቀም በተለይ ደግሞ የአማራ ሚዲያ ኮርፖሬሽንን ሬዲዮና ቴሌቪዥን በመጠቀም መልዕክቶችን አስተላልፈናል ነበር ያሉት፡፡

የሰላም ኃይማኖት የማይገድበው የሁሉም ጉዳይ በመሆኑ በባሕር ዳር ከተማ በሚገኙ ቀበሌዎችም የህብረቱ ቅርንጫፎች እንዲኖሩ በማድረግ የህብረቱ ዓላማ በጠንካራ መሰረት ላይ የቆመ እንዲሆን ለማድረግ ጥት አድርገናል በማለት መጋቢ ደሳለኝ ሀሳባቸውን አካፍለውናል፡፡

ሆኖም በሁለቱም እንግዶቻችን ዘንድ የተነሳው ሌላው ሀሳብ መስራት በሚገባን ልክ ሰርተናል ማለት አንችልም የሚል ሲሆን፤ ለዚህ ደግሞ ያነሱት ዋናው ምክንያት ጉባኤው ከመንግስት በኩል መታገዝ በሚገባው ልክ እየታገዘ ባለመሆኑ ነው፡፡ ማለትም በከተማው ብሎም በክልሉ ሰላም እንዲሰፍን የኃይማኖት አስተምህሮ ታላቅ ሚና አለው ተብሎ ከተቋቋመ በኋላ ብዙ ርቀት ሳይሔድ ትኩረት ተነፍጎታል ይላሉ፡፡

ለአብነትም የተጠናከረ ድጋፍና ክትትል አይደረግም፣ አመራሮች እንኳን የምንገናኝበትና ዶክመንቶችን የምናስቀምጥበት ቢሮ እንኳን ማግኘት አልተቻለም፡፡ በመሆኑም ቋሚ ይስብሰባ ጊዜ የለንም፣ በጀት ስለሌለን ከቦታ ቦታ ተንቀሳቅሰን አንዳንድ ተግባራትን ለመፈፀም የገዛ ኪሳችንን እየተጠቀምን በመሆኑ እንቅስቃሴያችን የተመጠነ እንዲሆን ስላደረገው ሊስተካከል ይገባል ብለዋል፡፡


የዝግጅት ክፍሉም በበኩሉ የሰላም ጉዳይ የቅድሚያ ቅድሚያ ሆኖ ካልተሰራበት በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ የጉዳቱ ተጋሪ ከመሆን ማምለጥ አይቻልም፡፡

ለዚህ ነው ባንድ ወቅት ማርቲን ሉተር ኪንግ "እንደ እህትና ወንድም በጋራ መኖርን መለማመድ አለብን ይህን ማድረግ ከተሳነን በጋራ እንጠፋለን" ያለው፡፡ ስለዚህ ሰላምን ለማምጣት ከታሪካዊ ቅራኔዎቻችን ይልቅ ለታሪካዊ መግባባታችን ቅድሚያ መስጠት ያስፈልጋል፡፡ ለዚህ ደግሞ ኢትዮጵያዊ በሙሉ እንደ እህትና እንደ ወንድም በአንድነት ለመነጋገር፣ ለመሥራት እንዲሁም በጋራ ለመጠቀም በንጹህ ልቦና መዘጋጀት ይኖርበታል፡፡

በዚህ ረገድ የጋራ አሸናፊነት መሳሪያ የሆነውን ሰላም ማንገብ ጠቀሜታው የጎላ ነው፡፡ በመሆኑም ሁሉም ኃይማኖቶች ያለልዩነት የሚያስተምሩት " ሰላም "ን ልንጠብቀውና ልንተቀምበት ይገባል እያልን ጽሁፋችንን በዚህ ቋጨን ሰላም።



" ቢቻላችሁ በእናንተ በኩል ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም ኑሩ"
( ወደ ሮሜ ሰዎች 12፡18 )



" ቢርቋችሁና ባይዋጉዋችሁ፣ወደ እንንተም ሰላም አላህ ለእናንተ በእነርሱ ላይ ( የመውጋት ) መንገድ አላደረገም፡፡ "
( ሱረቱ አን- ኒሳእ 4፡90 )

# “ሜዳውም ያው. . .”

በደፋሩ እምሬ

“ ኳስ ሜዳ ... ሆሆ ኳስ ሜዳ”

“ ኳስ ሜዳ ... ሆሆ ጨዋታ”

“ የተነፋፈቀው የሚተያይበት”

“ ተሰብስቦ አበሻ አንዴ ሚጎርፍበት”

“ ያሆሆ እንዴት ነው ኳስ ሜዳ”

“ያሆሆ የምንጨፍርበት።”

እያለች የኳስ ሜዳን ትዝታና ስሜት በሚቀሰቅሰው ማራኪ ድምጿ ታዋቂዋና ተወዳጇ አርቲስት አዚማለች።

በድምፃዊዋ ዘፈን ውስጥ “ኳስ ሜዳ፣ ጨዋታ፣ መሰባሰብ፣ሆሆ እያሉ መጨፈር፣ መደሰት” ተብለው የተጠቀሱት ጉዳዮች በተለያዩ የስፖርት ክዋኔዎች ላይ ሁሌም አብረው የሚኖሩና ለዚያ ክዋኔ መገለጫና ድምቀት ናቸው። ይሁን እንጅ “ከጋሪው ፈረሱ እንደሚቀድመው” ሁሉ “ኳስ ሜዳ” ከጨዋታ፣መሰብሰብ፣መጨፈርና መደሰት ቀድሞ መኖር ያለበት ጉዳይ ነው።

“ኳስ ሜዳ” ሲባል በብዙዎች አዕምሮ ቀድሞ የሚመጣው የእግር ኳስ ሜዳ የሚለው ነው። ይሁን እንጅ ይህ ስያሜ “ኳስ” በሚባለው ቁስ ጨዋታው የሚፈጸምባቸው ሌሎች የስፖርት አይነቶችን ለምሳሌ መረብ ኳስ ሜዳ፣ ቅርጫት ኳስ ሜዳ፣ ወዘተ. የሚገልፅ ይሆናል። ኳስን የማይጠቀሙ በርካታ የስፖርት አይነቶች እንደ ውሃ ዋና፣ ካራቴ፣ብስክሌት ውድድር፣ አትሌቲክስ፣ ወዘተ. “ኳስ ሜዳ” የሚለው መጠሪያ አይገልፃቸውም።

ከዚህ በተሻለ የሁሉም ስፖርት አይነት ጨዋታዎች የሚካሄዱባቸው የተለያዩ ሜዳዎች ”ስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች” ተብለው ቢጠሩ የተሻለ የሚያግባባ በመሆኑ እኛም ቀጥሎ በሚቀርበው የጽሁፉ ክፍል ሁሉ ይህንኑ የወል ወካይ መጠሪያ የምንጠቀም ይሆናል።



**አቶ ባንተአምላክ ሙላት**
“የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች ጤናማ የስፖርት ህብረተሰብ ለመፍጠር ሚናቸው የላቀ ነው”

ውድ አንባቢዎቻችን! ዛሬ ምነው ኳስ ሜዳ! ኳስ ሜዳ! ማለት አበዛችሁ በጹሁፍ ስፖርት ልታሳዩን ነው ወይስ ልታሰሩን? ማለታችሁ አይቀርም!።

እኛም እንላለን! ዛሬ ስፖርት አናሰራችሁምም ፤ አናሳያችሁምም። “መጀመሪያ መቀመጫየን” እንዳለችው እንስሳ ዛሬ የምንፈልጋችሁ ቅድሚያ ስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎችን መገንባት፣ማስፋፋትና ምቹ ማድረግ ስለሚያስፈልግ እንደ አማራ ክልል ይህን በመፈፀም ረገድ ማን ምን ድርሻ እንዳለው፣ ተግዳሮቶች ምንድን ናቸው?፣ የአጋር አካላት ተሳትፎ ምን ይመስላል? በሚሉትና በሌሎችም ተያያዥ ጉዳዮች ዙሪያ ባለሙያ ጋብዘን የሰጡንን ሰፊ ማብራሪያ መሰረት አድርገን ያዘጋጀነውን ጽሁፍ እንድታነቡ ነው።

አቶ ባንተአምላክ ሙላት ይባላሉ። በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ የስፖርት መገልገያ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ናቸው። መጀመሪያ ያነሳንላቸው ጥያቄ ከእርሳቸው ቢሮ ተግባርና ተልዕኮ አንጻር “ስፖርት ማዘውተሪያ ስፈራዎች እንዴት ይገለፃሉ?” የሚለው ሲሆን በምላሻቸውም፡- “ማንኛውም ህብረተሰብ በሚኖርበት፣ በሚሰራበትና በሚማርበት አካባቢ የቀለም፣ የዘር፣ የሀይማኖት፣ የፖለቲካ አመለካከት እንዲሁም የፆታና የእድሜ ልዩነት ሳይደረግ፣ ክልልና ድንበር ሳይወስነው ስፖርታዊ እንቅስቃሴዎችን፣ ስልጠናዎችንና ውድድሮችን

ለማከናዎኛነት የሚያገለግሉ አለማቀፍ ህግና ደንብ ተቀርፆላቸው የሚዘጋጁ መዝናኛዎችን ጭምር የሚያካትቱ መሆናቸውን” ገልፀዋል።

የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች ተብለው የሚጠቀሱ ናቸው ያሏቸውንም ሲዘረዝሩ 29 የፓራ ኦሎምፒክስ ፣ አትሌቲክስ ፣ የእግር ኳስ ፣ የቮሊቦል ፣ ቅርጫት ኳስ ፣ እጅ ኳስ፣ የጠረንጴ ኳስ፣የሜዳ ቴንስ፣ የጅምናስቲክ ስፖርቶች፣ የሞተር ስፖርቶች፣ የአለማቀፍ ቴኳንዶ፣ የጎልፍ ፣የቦክስ፣ የቼዝ ፣ እና የሌሎች ስፖርት አይነቶችም በዚህ ውስጥ እንደሚካተቱ ጠቁመዋል።

የህብረተሰቡን በተለይም የወጣቱን ጤንነት መጠበቅ፣አካል መገንባት፣አዕምሮ ማበልፀግ እና ለሀገር እድገት አስተዋፆኦ እንዲያበረክቱ ማስቻልን አላማው ያደረገው ስፖርት እውን የሚሆነው የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች በየአካባቢው በብዛትና በጥራት ሲኖሩ ነው። ይህንን ስፖርታዊ አላማ ለማሳካት ግማሽ መንገድ ይወስዳል ተብሎ የታሰበበት የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች የሚቋቋሙበት፣ የሚተዳደሩበት፣ ቁጥጥር የሚደረግበት እና ሕጋዊ ጥበቃ የሚያገኙበት ሁኔታን የሚደነግግ ሕግ ማውጣት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ አዋጅ ቁጥር 729/2004 ዓ.ም ሂደቱን ጨርሶ ተግባራዊ መደረግ ከጀመረ አመታት ተቆጥረዋል።



*በአማራ ክልል ከሚገኙ ቴኳንዶ ስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች አንዱ(ደብረ ማርቆስ ከተማ)*

ከዚህ ህግ አንፃር እንደ አማራ ክልል የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎችን የመለየትና የማልማት አሰራር ምን እንደሚመስልም ቀጥሎ በቀረበው መልኩ አብራርተዋል። "የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎችን የመለየት ጉዳይ ከመሬት ጋርም የተያያዘ ስለሆነ የስፖርት ተቋማት ብቻ ሳይሆኑ በመሬት አስተዳዳር ላይ የሚሰሩ አካላትንም ባሳተፈ መልኩ በከተማና በገጠር ቀበሌዎች ቢያንስ አንድ ማዘውተሪያ ስፍራ ሁሉንም ስፖርት አይነቶች በሚያሳትፍ መልኩ ከተለየ በኋላ ማስተር ፕላኑ በሚፈቅደው እና በማዘውተሪያ ስፍራዎች ስታንዳርድ መሰረት ከሶስተኛ ወገን ነፃ ሆኖ ይከለላል" ብለዋል።

ከላይ በተገለጸው መልኩ የተከናወነው የመለየት ስራ ወደ ማልማት የሚሸጋገር ሲሆን በመጀመሪያ ደረጃ በከተማ አካባቢ ለተለዩት ማዘውተሪያ ስፍራዎች ካርታና ፕላን፣ በገጠር አካባቢ ለሚገኙት ደግሞ የይዞታ ማረጋገጫ ከተሰጣቸው በኋላ ዙሪያቸው ቢያንስ በአጥር እንዲከለል ተደርጎ ዲዛይን ይሰራላቸዋል። እነዚህ እርምጃዎች ሁሉም የስፍራዎችን ህጋዊ የጥበቃ ዋስትና በዋናነት የሚያረጋግጡ ቢሆኑም በተዘጋጀላቸው ዲዛይን መሰረት ለተፈለገው የስፖርት አይነት በፍጥነት የልማት ግንባታቸው እንዲከናወን የሚጫዎተው ሚና ግን ከፍተኛ መሆኑን አስረግጠው ገልጸዋል።

"ማን ነው የሚያለማቸው?" የሚለው ጉዳይም ከላይ እንደተነሱት "እንዴት ይለያሉ?" እና "እንዴት ይለማሉ?" እንደሚሉት ጥያቄዎች ሁሉ ምላሽ የሚሻ ነው። በመሆኑም በቀበሌ፣በወረዳና በዞን ደረጃ ያሉት የማዘውተሪያ ስፍራዎች በዋናነት በአካባቢው መስተዳድር እና በህብረተሰቡ ተሳትፎ ይለማሉ። ለአገር አቀፍ፣ለአህጉር አቀፍና ለአለም አቀፍ ውድድሮች የሚያገለግሉና በክልል ዋና ከተማ ውስጥ የሚለሙ ማዘውተሪያ ስፍራዎች የክልሉ መንግስት በሚያደርገው ድጋፍ መሰረት የሚገነቡ ይሆናል። በዚህ ሂደት ውስጥ ባለሀቶብች፣የግል ድርጅቶች፣መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት፣የመሳሰሉት ባለድርሻ አካላት በንቃት ይሳተፋሉ። የአማራ ክልል ስፖርት ቢሮም በባለሙያና በገንዘብ በመደገፍ ስፍራዎች እንዲለሙ ሊሳተፍ እንደሚችል ጠቁመዋል።

"ነገርን ነገር ያነሳዋል" እንዲሉ አበው፣የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች በማን ይለማሉ ወይም ይገነባሉ በሚል የተነሳው ጥያቄ በክልሉ ምን ያህል የለሙ ወይም የተገነቡ ስፍራዎች ይገኛሉ የሚል ሌላ ጉዳይ ያስነሳል። ይህን ጉዳይ በሚመለከት ባለሙያው ሲያብራሩ ስታንዳርድ የሚያሟሉና የማያሟሉ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች በሚል በሁለት እይታ ተገምግመው ብዛታቸው እንደሚገለፅ ተናግረዋል።

ስታንዳርድ የሚያሟሉ የሚባሉት ለየስፖርት አይነቱ ስፍራዎች የተቀመጡ የተለያዩ መሰረታዊ መስፈርቶችን መሰረት አድርገው የተገነቡ ናቸው። ለምሳሌ የእግር ኳስ ስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራ ልኬታው ቢያንስ እና ቢበዛ ይህን ያህል ወርድና ርዝመት፣ቅርጹ አራት ማዕዘን ሬክታንግል መሆን አለበት ተብሎ የተወሰነለት አለማቀፍ የእግር ኳስ ሜዳ ስታንዳርዶች አለው። የጎሎቹ፣የመስመሮች አሰማመር፣ የሜዳው አቀማመጥ፣ወዘተ. ሁሉም ስታንዳርድ አላቸው።

አለማቀፉ የእግር ኳስ ፌደሬሽን ስታንዳርድ ናቸው ብሎ ያስቀመጣቸው ከልኬት፣ከገጽታ፣ ከምልክቶችና ከመሳሪያዎች ጋር ይያያዛሉ። ልኬትን በሚመለከት ሜዳው ለአለም አቀፍ ጨዋታዎች ከ100 እስከ 110 ሜትር ርዝማኔ እና ከ64 እስከ 75 ሜትር ስፋት እና አራት ማዕዘን ቅርጽ ያለው መሆን እንዳለበት ደንግጓል። ከዚህ በተጨማሪ 105 ሜትር በ 68 ሜትር እንደ ጥሩ መጠን አማራጭ እንደሚወሰድም ይመከራል። የገጽታ ጥራት ስታንዳርዶች ደግሞ ከተፈጥሮ እና ሰው ሰራሽ አረንጓዴ ሳር አኳያ የሚታዩ ናቸው።

የተፈጥሮው ሳር የተደላደለ ፣ አረንጓዴ የሆነ፣ ደረጃውን የጠበቀ ፣ጥሩ የፍሳሽ ማስወገጃ፣ስሩ ጥልቀትና ጥንካሬ ያለው መሆን ይገባዋል። ሰው ሰራሽ ሳሩ ደግሞ በፊፋ የተረጋገጠ ሆኖ ወጥ የሆኑ ቃጫዎች ያለው፣ኳስን በጥሩ ሁኔታ የሚያንከባልል እና የዝናብ ውሃን በፍጥነትና በደንብ መምጠጥ የሚችል መኖን ይኖርበታል። ይህ የፊፋ መስፈርት ወይም ስታንዳርድ የሳር ቴክኖሎጂ እድገትን የሚያሳይ ነው። ምልክቶች በፊፋ ዘንድ አለማቀፍ የእግር ኳስ ሜዳ ስታንዳርዶች ናቸው። የመጫወቻው መስክ አራት ማዕዘን እና በመስመሮች ምልክት የተደረገበት መሆን አለበት.። ረዣዥም መስመሮች የንክኪ መስመሮች ተብለው የሚጠሩ ሲሆን አጫጭር መስመሮች ደግሞ የግብ መስመሮች ይባላሉ። የመስመር ምልክቶች በፊፋ ህጎች መሰረት ከ12 ሴንቲ ሜትር ያልበለጡና በጨዋታ ልኬቶች መስከ

ውስጥ መሆን አለባቸው። የመስመር ምልክቶች ግልጽ እና ትክክለኛ ሊሆኑ ይገባል።

መሳሪያዎች እንደ አንድ የአለማቀፍ የእግር ኳስ ሜዳ ስታንዳርድ አካል ሆነው የሚወሰዱ ሲሆን ሜዳውን ለማስዋብና ለመጠገን የሚውሉ ተሽከርካሪዎችና ቴክኖሎጂዎች ይጠቀሳሉ። እነዚህን ስታንዳርዶች ከሞላ ጎደል ያሟላሉ ተብለው የሚወሰዱት የክልሉ ሁለት ለእናቱ ስታዲየሞች የወልዲያ ስታዲየምና የባህር ዳር አለም አቀፍ ስታዲየም ናቸው።

ወልዲያ ስታዲየም በሰሜኑ ጦርነት ወቅት ከፍተኛ ውድመት ስለደረሰበት የክልሉ መንግስት የጉዳት መጠኑን በማጥናት ጥገና ለማድረግ እየተንቀሳቀሰ ሲሆን በቅርቡ ጥሩ ጥገና ተደርጎለት አገር አቀፍና አለም አቀፍ ውድድሮችን እንዲያስተናግድ ይሆናል። የባህር ዳር አለም አቀፍ ስታዲየም ደግሞ በአሁኑ ወቅት ሁለተኛው ምዕራፍ ግንባታ እየተጠናቀቀ ይገኛል። ይህ የግንባታ ምዕራፍ ስታዲየሙ የካፍና የፊፋ መስፈርቶችን እንዲያሟላ ስለሚያደርገው አለም አቀፍ ውድድሮችን ወደ ማስተናገድ ደረጃ ያሳድገዋል።

የሌሎች ስፖርት አይነቶች ማዘውተሪያ ስፍራዎችም እንደ እግር ኳስ ሜዳው ሁሉ ሳይንሳዊ የሆኑ በርካታ ስታንዳርዶችን አሟልተው ይለማሉ ወይም ይገነባሉ። ከዚህ ትርጓሜ በተቃራኒ ያሉት ስፍራዎች ሁሉም ስታንዳርድ የማያሟሉ ወይም ከስታንዳርድ ውጭ የሆኑ በሚል ይገለፃሉ። ለአብነት ያህል አስፓልት መንገድ አዘግቶ እግር ኳስ መጫዎት ስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራ ሊሆን አይችልም። አንድ ጠበብ ባለ ባዶ ቦታ ወይም በስፖርት ተቋም እውቅና በሌለው ሜዳ ላይ ወጣቶች እንደነገሩ መስመር ሰርተውለት፣ጎሎችን በድንጋይ ወስነው አዘውትረው የተለያዩ ስፖርቶችን የሚሰሩበት ስታንዳርድ የማያሟላ ስለሆነ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራ ሊባል አይችልም። ከዚህ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች ስታንዳርዳዊ ትንታኔ አኳያ ከተሰበሰበ ቆየት ያለ አሀዛዊ መረጃ እንደሚያሳየው በአማራ ክልል በጥቅሉ ከሶስት ሺህ 400 በላይ ስታንዳርዶችን አሟልተውና ለምተው የተለያዩ የስፖርት አይነቶችን አገልግሎት እየሰጡ ያሉ ይገኛሉ። በክልሉ ያለውን ወቅታዊ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች በአይነት አሀዛዊ መረጃ ቆጠራ ለማካሄድ ቅድመ ዝግጅት ተጠናቆ ስራው ሊጀመር ስለሆነ ቆጠራው ሲጠናቀቅ ወደፊት መረጃን ለህዝብ ይፋ የምናደርግ ይሆናል ብለዋል።

የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች ጭራሽ አለመኖር ብቻ ሳይሆን ኖረውም ለየስፖርት አይነቶች አስፈላጊ ናቸው የሚባሉት የማቴሪያልና የቴክኖሎጅ ግብዓቶች በወቅቱ ስለማይሟሉ ለታለመላቸው አገልግሎት ሳይውሉ የተቀመጡ ብዙ ናቸው። ይህን ችግር የመቅረፍ ሃላፊነት የተሰጠው የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች ባሉበት አካባቢ የሚገኘው አስተዳደር፣ ህዝብና ተቋም ነው። እነዚህ አካላት ስፍራዎችን የመለየት፣የመገንባትና የማልማት እንዲሁም ህጋዊ ማረጋገጫ የመስጠት ሀላፊነት ያላቸው መሆኑ ቀደም ሲል መገለጹ ይታወሳል።

ስፍራዎች በአግባቡ መገንባታቸውን ፣ መልማታቸውንና በሁለንተናዊ መልኩ ለስልጠናና ውድድር ምቹ በማድረግ በኩል ደግሞ በወረዳ፣በዞንና በክልል ደረጃ ያሉ አካላት ተገቢውን ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ለህብረተሰቡ ሙሉ አገልግሎት እንዲሰጡ ያመቻቻሉ። ይህ ካልሆነ "ወጣ ወጣና እንደሸንበቆ ተንከባለለ እንደሙቀጫ" ነው የሚሆነው። በዚህ ሁሉ መካከል የክልሉ ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ሙያዊ ክትትልና ድጋፍ እንዲሁም የቁሳቁስ እገዛ የሚያደርግባቸው አጋጣሚዎች እንዳሉም ባለሙያው ጠቁመዋል።



*በአማራ ክልል ከሚገኙት የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች አንዱ*
*(ወልዲያ ስታዲዬም)*

የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎችን በመለየት የጀመረው ይህ ጽሁፍ ለስልጠናና ውድድር ምቹ አድርጎ “ሜዳውም ያው…” ደረጃ ላይ ደርሷል። ከዚያስ? የሚለው ጥያቄ ቀጥሎ የሚነሳ ሲሆን ከተጫዋቾች አንጻር ተዳሶ የሚመለስ ይሆናል። እንደሚታወቀው ለየትኛውም የስፖርት አይነት የሚሆኑ ማዘውተሪያ ስፍራዎች ተሟልተው ዝግጁ ከሆኑ በኋላ ተጫዋቾች ስለሚያስፈልጉ እነሱን መመልመል፣ማሰልጠንና ማደራጀት ታቅዶና ትኩረት ተሰጥቶት ይሰራል። ለዚህ ተግባር ስኬት እንደ ዋና ማሳለጫ ተደርጎ የተወሰደው የስፖርት ክለቦችን አቋቁሞ ተቋማዊ ቅርፅ አስይዞ ማስቀጠል ነው።

ክለቦች በመንግስት፣በልማት ድርጅቶችና በግለሰቦች ሊቋቋሙ ይችላሉ። መንግስት በከተሞች፣በወረዳዎች፣በተለያዩ መስሪያ ቤቶች ለአብነት በማዘጋጃ ቤቶች ብዛት ያላቸው ክለቦች ይቋቋማሉ። እንደ ፖሊስ ያሉ ተቋማትም ክለቦችን በማቋቋም ይታወቃሉ።

የልማት ድርጅቶች እንደ ውሃ ስራዎች ኮርፖሬት፣ባንኮች፣ጥረት፣ የመሳሰሉት ክለቦችን በማቋቋም ለስፖርቱ እድገትና ተተኪዎችን የማፍራት ድርሻቸውን እየተወጡ ይገኛሉ። በግለሰብ ደረጃም ክለቦችን እያቋቋሙ ስፖርቱን ይደግፋሉ። ለምሳሌ አቶ ባለይነህ ክንዴ ያቋቋሙት የአትሌቲክስ ክለብ አላቸው። "የትም ፍጭው…” ነውና ነገሩ ክለቦች በማንም ይቋቋሙ ዋናው የሚፈለገው ስፖርቱን ተቋማዊ መልክ አስይዞ በማደራጀት እንዲያድግ ማድረጋቸው ነው።

በአማራ ክልል ከላይ በተገለጹት አካላት እና በሌሎችም አማካኝነት በተለያዩ የስፖርት አይነቶች የተቋቋሙ ክለቦች ብዛት ከ300 በላይ ይሆናሉ። እነዚህ ክለቦች በፕሪሚየር ሊግ፣በከፍተኛ ሊግ፣በአንደኛ ሊግና በአማራ ሊግ ደረጃ የተቋቋሙ ናቸው። ባቋቋማቸው አካል በየአመቱ በጀት እየተመደበላቸው ለስፖርተኞች፣ለአሰልጣኞችና ለድጋፍ ሰጭ ሰራተኞች ደመወዝ በመክፈል ውድድር ሁሉ ያካሂዳሉ።

ክለቦች የሚያቅፏቸውን እና ለውድድር የሚያዘጋጇቸውን ስፖርተኞች የሚመርጡበትና ስፖርተኞችን የሚመለምሉበት አሰራርና ማን ሀላፊነት ወስዶ እንደሚሰራው ተለይቶ ይታወቃል። በታዳጊ ወጣቶች ስልጠና ፕሮጀክት ምልመላ ታዳጊዎች በችሎታቸው መሰረት በአሰልጣኞቻቸው ይመረጣሉ። ለተለያዩ ስፖርት አይነቶች ስልጠና ምልመላ የሚደረገው መምረጫ መስፈርቶች ወጥተው ለዞኖች ኮታ ይሰጥና በዚያ መንገድ ዞኖች በማወዳደር ይመርጣሉ። ወደ ክለብ የሚገቡ ስፖርተኞችን መረጣ በሚመለከት ሙሉ በሙሉ የክለብ አሰልጣኞችና የክለብ ቦርድ አመራሮች የተለያዩ መስፈርቶችን በመጠቀም ይመርጣሉ ብለዋል።

ውድ አንባቢዎቻችን! ከላይ ባነበባችሁት የጽሁፉ ክፍል ውስጥ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎችን በመለየት፣ በማቋቋም፣ በማልማትና በማደራጀት ሂደት ላይ አወንታዊ አፈጻጸሞችንና ስኬቶችን ብቻ ስትመለከቱ፤ ተግዳሮቶች የሉም እንዴ? የሚል ጥያቄ በውስጣችሁ መመላለሱ አይቀርም። እውነት ነው! ተግዳሮት የሌለበት ስኬት አይኖርም። ስኬቶች ካሉ ተግዳሮቶችም አሉ። ግለሰቦችም ሆኑ ድርጅቶች ግቦቻቸውን የሚያሳኩት ተግዳሮቶችን ጠንክረው ተቋቁመው በማለፍ ነው። ለዚያም ነው የስነ ልቦና ምሁራን “ተግዳሮቶች የጥንካሬና የስኬት ምንጭ ናቸው” ሲሉ የሚደመጡት። ይህን ተጠየቅ ስለ ስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች ከተነሳው ጉዳይ ጋር ተያይዞ ያጋጠሙትን ተግዳሮቶች ባለሙያው አንድ፣ ሁለት፣ ሶስት ብለው ዘርዝረዋቸዋል።

የመጀመሪያው ተግዳሮት የአካባቢው መስተዳድር መሬት ለመስጠት ፈቃደኛ ሆኖ አለመገኘት ነው። የዚህ ችግር መነሻው መሬት የሌለ ሆኖ ሳይሆን ለስፖርት ቅድሚያ አለመስጠ መሆኑ ታይቷል። የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች በአየር ላይ የሚንሳፈፉና የሚገነቡ ይመስል መሬት ለመስጠት ፈቃደኛ አለመሆን በብዙ አካባቢዎች አለ።

እንደሚታወቀው የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች እንዲቋቋሙ በሚደረጉባቸው ገጠር አካባቢዎች፣ ቀበሌ፣ ወረዳ፣ ዞንና ክልል መሬት የሚያቀርበውና የሚገነባው የየአካባቢው መስተዳድር ህዝቡን አስተባብሮ እንደሆነ ማቋቋሚያ አዋጁ ያስገነዝባል።

ለስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች ህጋዊ ካርታ ወይም ማረጋገጫ ደብተር በወቅቱ ካለመስጠቱ ጋር ተያይዞ ወሰናቸውን ማስከበር አለመቻል ሁለተኛው ተግዳሮት መሆኑን ባለሙያው አንስተዋል። አዋጅ ቁጥር 729/2004 ዓ.ም አንቀጽ ዘጠኝ ንዑስ አንቀጽ አንድ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎችን ከልሎ ስለመያዝ ይደነግጋል። እናም ይህን ቶሎ ያለመፈፀም ተግዳሮት ሆኖ መገኘቱን ተናግረዋል።

ለስፖርታዊ እንቅስቃሴ፣ ሥልጠና፣ ውድድር፣ መዝናኛ ወይም ለስፖርታዊ በዓል ማከናወኛነት ለሚሉት አላማዎች እንዲውል የተዘጋጀ ማንኛውም ሥፍራ "የስፖርት ማዘውተሪያ" እንደሚባል አዋጅ ቁጥር 729/204 አንቀጽ ሁለት ንዑስ አንቀፅ ሁለት ላይ በትርጓሜ ክፍል ላይ ተደንጓል። የዚሁ አዋጅ አንቀፅ ስምንት ደግሞ በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣው ደንብ ለሚዘረዘሩ ሌሎች ተዛማጅ ዓላማዎች ብቻ የሚውሉ ይሆናል ይላል፡፡ ይሁን እንጅ እነዚህን ድንጋጌዎች በጣሰ መልኩ ነባር ማዘውተሪያ ስፍራዎችን ነጥቆ ለሌላ አገልግሎት አሳልፎ መስጠት ተግዳሮት ሆኖ ይስተዋላል ብለዋል።

አቶ ባንተአምላክ አምስተኛ ተግዳሮት ነው ብለው ያነሱት ጉዳይ ደግሞ ስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች የደረጃ ማሻሻያ ስለማይደረግላቸው ለአገር ውስጥና አለማቀፍ ውድድሮችና ስልጠናዎች ብቁ ወይም ምቹ አይደሉም የሚለው ነው። ይህ ተግዳሮት ከላይ ከተገለፀው አዋጅ አንፃር ምን ያህል የሚጋጭ መሆኑንም ለማሳየት ሞክረዋል።

በአዋጁ አንቀጽ አራት ንዑስ አንቀጽ አንድ ላይ ማንኛውም የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራ ኮሚሽኑ በሚያወጣው መመሪያ



በስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራ የጅምላ ስፖርት ሲደረግ (እንጅባራ ከተማ)

መሠረት ለታቀደለት አገልግሎት ብቁ የሚያደርጉትን መሠረታዊ መሥፈርቶችን የሚያሟላ መሆን እንዳለበት ይደነግጋል፡፡

ከደረጃቸው አንፃርም ዓለም አቀፍ የስፖርት ውድድሮችን ለማስተናገድ ብቁ የሚሆኑት በደረጃ አንድ፣አገር አቀፍ የስፖርት ውድድሮችን በደረጃ ሁለት እና ለክልል አቀፍ ብቁ የሚሆኑት ደግሞ በደረጃ ሦስት ይመደባሉ (ሶስቱም ደረጃዎች በንዑስ አንቀጽ አንድ የተጠቀሱትን መሥፈርቶች ሟሟላት እንዳለባቸው ልብ ይሏል) በማለት ገልጸዋል።

በመጨረሻ ያነሳንላቸው ጥያቄ የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራዎችን የመለየት፣ የማስፋፋት፣ የመገንባት፣ የማሟላትና ከዚሁ ጎን ለጎን የሚያጋጥሙትን ተግዳሮቶች ሁሉ ተቋቁሞ ስፍራዎችን ለታቀደላቸው አላማ ለማዋል እነማን በዚህ ዙሪያ ምን ድርሻ ያበረክታሉ የሚለውን በዝርዝር እንዲያብራሩልን ነው። እሳቸውም ገለፃቸውን የጀመሩት ከራሳቸው ተቋም ሲሆን የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች ጉዳይ በዋናነት ተግባሩና ሃላፊነቱ በየደረጃው ላለው ወጣቶችና ስፖርት ተቋም መሆኑን በማመላከት ነው።

ነባሮችንም ሆነ አዲስ የተገነቡትን የተለያዩ አይነት ስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራዎች ደረጃ በማውጣት ለክልል፣ለአገር አቀፍና አለማቀፍ ስልጠናዎችና ውድድሮች ብቁና ምቹ እንዲሆኑ ድጋፍና ክትትል በማድረግ ለሙሉ አገልግሎት ያዘጋጃል። ሌላው የተቋሙ ተግባር የተነጠቁ ማዘውተሪያ ስፈራዎችን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ያስመልሳል። ይህም በአዋጅ ቁጥር 729/2004 ዓ.ም አንቀፅ 10 ላይ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች ሕጋዊ ጥበቃ እንዲደረግላቸው የተደነገገውን መሰረት በማድረግ እንደሚፈፀም ገልጸዋል።

ሌላው አካል መንግስት ነው። መንግስት ከማንኛውም አካል የበለጠ የመምራት፣ የመደገፍ፣የመከታተል፣የመፈጸም፣ወዘተ. ግዙፍ አቅም ያለው ስለሆነ ከሞላ ጎደል ከስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራዎች ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን ማሳካት ይችላል። በእርግጥ ወጣቶችና ስፖርት ተቋም የመንግስት መስሪያ ቤት ስለሆነ የመንግስትን የስፖርት ፖሊሲዎች፣ እቅዶች፣ወዘተ. ታች ድረስ ባለው መዋቅሩ ስለሚፈፅም መንግስት እንደሰራው ተደርጎ ይወሰዳል።

ህብረተሰቡ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች በየአካባቢው በብዛትና በጥራት እንዲስፋፉና እንዲጠበቁ በማድረግ በኩል ከፍተኛ ድርሻ አለው። ይህን ድርሻውን በአግባቡ የሚወጣ ህብረተሰብ ደግሞ በሚኖርበት፣ በሚማርበትና በሚሰራበት አካባቢ በስፖርት እንቅስቃሴ ተሳታፊ የሚሆንበትን እና "የስፖርት ማህበረሰብ" የሚፈጠርበትን ሁኔታ ስለሚያመቻች ከስፍራዎች ከፍተኛውን አገልግሎት እንዲያገኙ ያግዛል፡፡ በተለይ ወጣት ከሚባለው የእድሜ ክልል በላይ ያሉ የህብረተሰብ ክፍሎች እድሜ እየጨመረ ሲሄድ ሊከሰት የሚችለውን ያልተገባ ውፍረትና የጤና መታወክ ለመከላከል የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች በየአቅራቢያው ምቹ ሆነው መገኘታቸው በግል፣በቡድንና በጅምላ የስፖርት እንቅስቃሴን ለማዘውተር ከፍተኛ ተነሳሽነትን ይፈጥራሉ ብለዋል።

"ማንን ይዞ ጉዞ" እንደሚባለው የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች ያለ ወጣቶች ተሳትፎ እንዲስፋፉና እንዲጠበቁ ማድረግ በአንድ እጅ እንደማጨብጨብ ይቆጠራል። ወጣቶች በገንዘብ፣ በጉልበት፣ በእውቀት ተሳትፎ በማድረግ ስፍራዎችን በመገንባት፣

በማልማትና በመጠበቅ ለማንኛውም የስፖርት አይነት ብቁ እንዲሆኑ በማድረግ በኩል የጎላ ድርሻ አላቸው። በተጨማሪም ወጣቶች በተለያዩ ውድድሮችና ስልጠናዎች ላይ በመሳተፍ ጤንነታቸውን በመጠበቅ፣ አካላቸውን በመገንባት፣ አዕምሯውን በማበልፀግ እና ለሀገር እድገት አስተዋፆ በማድረግ በኩል በንቃት በመሳተፍ ቀዳሚ መሆን እንደሚያደርጋቸውም ተናግረዋል።

ለስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች እውን መሆን ድርሻ ያላቸውና "አጋር አካላት" በሚል የሚጠሩም አሉ። እነዚህ አካላት ሁሉም የመንግስት ተቋማት ሲሆኑ ለስፍራዎች መሬት በማቅረብ የድርሻቸውን የሚያበረክቱ የየአካባቢው የከተማ እና የገጠር ቀበሌ አስተዳደሮች ይጠቀሳሉ። በገጠር አካባቢ ለሚስፋፉ ማዘውተሪያ ስፍራዎች የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ደብተር በመስጠት በኩል መሬት አስተዳደርና ግብርና ቢሮ የበኩላቸውን አስተዋፅኦ የሚያበረክቱ አካላት ናቸው። በከተማ ለሚስፋፉት ደግሞ ካርታና ዲዛይን በማዘጋጀት ማዘጋጃ ቤቶች መልካም አሻራቸውን እያስቀመጡ ይገኛሉ።

በተሰጣቸው መሬት ላይ በዲዛይናቸው መሰረት በመገንባት ለመጨረሻው ተጨባጭ እውንነት በማብቃት ድርሻውን በማበርከት ከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ቢሮ ጥሩ አጋር አካል ሆነው በክብር እንደሚጠቀሱ ገልጸዋል ይወሳል።

ጠቅለል ተደርጎ ሲታይ "አንድነት ሀይል ነው" እንደሚባለው እነዚህ አጋር አካላት እና ቀደም ሲል የተጠቀሱት የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ያላቸው የእውቀት፣የገንዘብና የጉልበት ሀይል የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎችን በከተማና በገጠር በመገንባት፣በማልማትና በማሟላት ለየስፖርት አይነቶች ምቹና ብቁ በማድረግ በኩል ከበቂ በላይ ሆኖ እያለ አሁንም በአማራ ክልል የስፍራዎች እጥረት ይስተዋላል። በመሆኑም ወደፊት ይህን ትልቅ አቅም በአግባቡ በመጠቀም ከማዘውተሪያ ስፍራዎች ጋር የተያያዘውን ችግር ለማስወገድ ትኩረት ሰጥቶ መረባረብ ይገባል። የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች እዚህም እዚያም መበራከት በተለይ ወጣቶች አካላዊ እንቅስቃሴዎቸን በማድረግ እየተዝናኑ ጊዜያቸውን በጥሩ ሁኔታ በማሳለፍ ተጠቃሚ ሊሆኑ ይገባል።

አሁን ላይ ወጣቶችን የሚጎዱ አደንዛዥ እፆችና አሉታዊ መጤ ልማዶች የተበራከቱባቸው አልባሌ ቦታዎች ስላሉ ወደእነዚያ በመሳብ ለሱስ እንዳይጋለጡ በመከላከል በኩል የሚጫወቱት ሚና ከፍተኛ ነው። በመሆኑም የክልሉን ወጣቶች በማወያየት በብዛትና በንቃት አንቀሳቅሶ የስፖርት ማዘውተሪያዎችን በማስፋፋት ብቻ ሳይሆን ስፖርት የሚዘወተርባቸውም በማድርገ ረገድ ከመቸውም ጊዜ በላቀ ደረጃ ትኩረት ሰጥተን መስራት ይኖርብናል። የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎችን ለይቶ ለመስጠት ቢሮክራሲ የሚያበዙ፣ ከናካቴው መሬት የማይሰጡ አካላት መታረም አለባቸው። ህብረተሰቡም የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎችን እንደ ጤና ተቋማት ሁሉ ተጨማሪ የጤናው መጠበቂያ አድርጎ በመቁጠር መንከባከብ ይጠበቅበታል፤ የሚል መልዕክት በማስተላለፍ አቶ ባንተአምላክ ገለፃቸውን ቋጭተዋል።

እኛም መረጃ በመስጠት የተባበሩንን ሁሉ እጅ እየነሳን እና ለስፖርት ማህበረሰቡ "ሜዳውም ያው ጨዋታውም ያው" እያልን ስፖርት ለአካላዊ ጥንካሬ እና ጤናማ ትውልድ ከመገንባት አንፃር ያለው ፋይዳ ትልቅ መሆኑን ተገንዝበን ስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎችን በማስፋፋትና በመጠበቅ በኩል በንቃት መሳተፍ ይገባናል እያልን ተሰናበትን—ሰላም!



# በጐነት...

በሳሮን ስማቸው

"ሰውን ለመርዳት ሰው መሆን በቂ ነው" የሚለው ሀሳብ ተዘውትሮ ሲነገር ይደመጣል፡፡ በአለማዊው አስተምሮ የፍልስፍና ትርጓሜም እየተሰጠው መረዳዳት ለሰው ልጅ የተሰጠ ፀጋ ብቻ ነው የሚል እሳቤን ያንፀባርቃል፡፡ ወይም ደግሞ የሰው ልጅ ሰውን ለመርዳት የተፈጠረ ሰባዊ ፍጡር ነው የሚልም ግብራዊ ትርጓሜ ይይዛል፡፡

በእምነታዊ ወይም ሀይማኖታዊ አስተምሮ ደግሞ ሰውን መርዳት የጽድቅ በረከትን በማግኘት ወደ ገነት የሚያስገባ መልካም ስራ ተደርጎ የሚታሰብ ነው፡፡ "... ቢኖርም ባይኖርም ከክፉት በጐነት ሳይሻል አይቀርም" ሲባልም የሚደመጠው ለዚህ ነው፡፡ በጐነት መቼም ቢሆን የሰው ልጅ በህይወት እስካለ ድረስ የህይወት መርሁ አድርጎ ቢተገበረው እንደሚመረጥም ይታመናል፡፡

በጐነትን በዚህ መልኩ ለመነሻ ያህል በአጭሩ ለመግለጽ ተሞከረ እንጅ ወደ ትልቅ የአገልግሎት ኢንዱስትሪ አድጐ "የበጐ ፈቃድ አገልግሎት" የሚል ስያሜ ተሰጥቶት አለምአቀፍ ጉዳይ ሆኖ ግለሰቦች፣ ድርጅቶች፣ አገራት ወዘተ. በተለይ ሰዋዊ በሆኑ በርካታ ዘርፎች ላይ እውቀታቸውን፣ ገንዘባቸውን፣ ጉልበታቸውን እና ጊዜአቸውን በራሳቸው ፈቃድ በማፍለስ በሚሊዮን እና በቢሊዮን የሚቆጠሩ የአለም ሰዎችን ሲረዱ፣ ሲንከባከቡ፣ ሲያበሉ፣ ሲያለብሱ ወዘተ. ውለው ያድራሉ፡፡ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት አስተማሪነቱ ሚዛን የሚደፋ ሊነገር የሚገባው ጉዳይ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በእነማንና በምን ምክንያት ተጀመረ? የሚለውን አለማቀፋዊ ታሪኩን? በኢትዮጵያና በተለይም በአማራ ክልል አጀማመሩን እና በክልሉ የበጎ አድራጎት ስራ ያለበት ነባራዊ ሁኔታ ምን እንደሚመስል፣ የሚሰጡት አገልግሎቶች ምን ምን እንደሆኑ፣ በእነማን እንደሚሰጡ፣ የሚሉትንና ሌሎችንም ተያያዥ ጉዳዮችን አስመልክቶ የአማራ



**አቶ ዘላላም አረጋ**

"በጎነት ለራስ ነው"

ክልል ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ምክትል ቢሮ አላፊ ከሆኑት ከአቶ ዘላላም አረጋ ጋር የነበረንን ቆይታ ለዚህ አምድ በሚመጥን መልኩ አቀናብረን አቅርበነዋል- መልካም ንባብ፡፡

**ህዳሴ፡-** ለዚህ ቃለ ምልልስ ፈቃደኛ ስለሆኑ በመጀመሪያ እናመሰግናለን፡፡

**እንግዳለ፡-** እኔም አክብራችሁ ስለጋበዛችሁኝ አመሰግናለሁ፡፡

**ህዳሴ፡-** ለመነሻ እንዲሆነን "በጐ ፈቃድ አገልግሎት" ማለት ምን እንደሆነ ቢያብራሩልን?

**እንግዳ፡-.** በጎ ፈቃድ አገልግሎት ማለት የህዝቦች ቅንነት፣ሰባዊ አመለካከትና በጎ የሆነ የለውጥ ፍላጎት በእጅጉ የሚሻና ወጣቱ የሀገርና የህዝብ ሃላፊነትን በመወጣት መልካም ስነ-ምግባርንና ስብዕናን ተላብሶ የበኩሉን አስተዋፅዖ እንዲያበረክት የሚያስችል በጎ ተግባር ነው፡፡ ቢሮው በባለፉት አመታት በተለያዩ የስራ መስኮች ወጣቶችን በስፋት በማሰማራት ልዩ ልዩ የህብረተሰብ ክፍሎችን ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡

በጎ ፈቃደኝነት ጭንቀትንና ድብርትን በመቀነስ ደስታን ለመጨመር ይረዳል። እንደ ኦክሲቶሲን እና ዶፓሚን ያሉ "የጥሩ ስሜት" ሆርሞኖች እንዲለቀቁ ያነሳሳል፡፡ አጠቃላይ የአእምሮ ደህንነትን በማሻሻል ጥሩ ስሜት እንዲሰማን ይረዳናል፤ ማህበራዊ ግንኙነቶችንም ያጠናክራል፡፡ በጎ-ፈቃደኝነት አዳዲስ ሰዎችን ለመገናኘት፣ ማህበራዊ ግንኙነታችን ለማስፋት እና የማህበረሰብ ቁርኝታችን ለማዳበር ጥሩ መንገድ ነው። በጐ ፍቃደኛ ስንሆን ተመሳሳይ እሴቶችን ከሚጋሩ ሰዎች ጋር ጠንካራ ግንኙነት ለመፍጠር ይረዳናል።

ከዚህ በተጨማሪ በጎ-ፈቃደኝነት እንደ አመራር፣ ግንኙነት፣ የቡድን ስራ እና ችግር መፍታት የመሳሰሉ አዳዲስ ክህሎቶችን ለመማር እና ለመለማመድ እድሎችን ይሰጣል። እነዚህ ችሎታዎች የስራ ልምድ እና የስራ እድል ከፍ ሊያደርጉ ይችላሉ፡፡ በተለይ በተዛመደ መስክ በቂ የሆነ ልምድ ለመጨበጥ ድርሻው የጎላ ነው፡፡

**ሐዲስ፡-** የበጎ ፈቃድ አገልግሎት አጀማመሩ ምን እንደ ሚመስል ቢገልጹልን? በማን ተጀመረ?

**እንግዳ-፡-** በዓለም ዓቀፍ ደረጃ በጎ ፈቃድ መቼ እንደ ተጀመረ የሚያመላክት መረጃ ባይኖርም የረጅም ጊዜ ታሪክ እንዳለው አመላካች ተግባራት አሉ።

ያም ሆኖ ጅማሮው በአሜሪካን አገር እንደነበር ይወሳል። ምክንያቱ ደግሞ የእርስ በእርስ ጦርነት ወቅት «የፈቃደኛ ቡድን» የተሰኘ ስያሜ ያላቸውና ቁጥራቸው የተበራከተ ሴቶች ለወታደሮችና ለጦር ጉዳተኞች ጊዜያቸውን ሰውተው ነፃ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት መስጠታቸው ነው። እኤአ በ1881 ባርተን የአሜሪካ ቀይ መስቀልን ሲመሰርት እኤአ በ1889 ደግሞ በጆንስተውን የውሃ መጥለቅለቅ ለተጎዱ ሰዎች እርዳታዎችን በማሰባሰብ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት

ተጀምሯል፡፡ በዚህ ተሳትፎ ከሌሎች የሕብረተሰብ ክፍሎች ይልቅ ሴቶች አይነተኛ ሚና ተጫውተዋል፡፡ ለዚህም ነው በጎ ፈቃድ አገልግሎትን? ሴቶች ጀምረውታል የሚባለው፡፡ በዚህ መሰረት በአለም አቀፍ ደረጃ በየዓመቱ በተለያዩ የበጎ ፈቃድ መስኮች ከአንድ ቢሊዮን በላይ ሰዎች እንደሚሳተፉ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የበጎ ፈቃደኞች ማስተባበሪያ መረጃ ያሳያል፡፡አለም አቀፍ በጎ ፈቃደኝነት፣ በታሪክም "ኤክስፖርት በጎ ፈቃደኝነት" እና "የባህር ማዶ በጎ ፈቃደኝነት" በ20ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ በእውቀት ሰጭ ትምህርት፣ በሃይማኖታዊ ትምህርት እና በአደጋ ማገገሚያ ጥላ ስር እንደ እንቅስቃሴ ተጀመረ፡፡

በአንደኛው የዓለም ጦርነት ለደረሰው ጉዳት እና ውድመት ምላሽ ስራ ካምፕ እንቅስቃሴዎች እና ቀደምት የሚስዮናውያን አገልግሎት በዓለም አቀፍ ደረጃ የመጀመሪያ መግለጫዎች ነበሩ፡፡ እ.ኤ.አ. በ 1920 ዎቹ ውስጥ ዓለም አቀፍ የሥራ ካምፖች እና የበጎ ፈቃደኞች ሠራዊት ከጦርነት ሰላማዊ አማራጮች ሆነው ተቋቁመዋል ፡፡

ዓለም አቀፍ ግንዛቤን ለማስተዋወቅ እና በአደጋ እና በጦርነት የተጎዱ አካባቢዎችን መልሶ ለመገንባት ሰርቪስ ሲቪል ኢንተርናሽናል የተባለ አንጋፋ ዓለም አቀፍ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ድርጅቶች አንዱ በ1934 ተመሠረተ፡፡ ይህ እንቅስቃሴ እ.ኤ.አ. በ1944 የብሬተን ውድስ ተቋማትን እና በ 1945 የተባበሩት መንግስታትን ጨምሮ ከትላልቅ ተሻጋሪ ተቋማት እድገት ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ በዚህ ዓለም አቀፍ የትብብር ሥርዓት ውስጥ ነበር አብዛኞቹ በመንግሥት የሚደገፉ ዓለም አቀፍ የበጎ ፈቃድ ትብብር ድርጅቶች (IVCOs) ብቅ ማለት የጀመሩት፡፡ በጎፈቃድ አገልግሎት ፅንሰ ሀሳብ እንደየ ኅብረተሰቡ የዕድገት ደረጃ እና አካባቢያዊ ሁኔታ በመለያየቱ አንድ ወጥ ትርጉም ላይኖረው ይችላል፡፡

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ግን የበጎ ፈቃድ አገልግሎትን "የሁሉም የማኅበረሰብ አካል የሥልጣኔ ውጤት ነው" ይለዋል፡፡

ፅንሰ ሀሳቡ ሲተነተን የበጎ ፈቃድ አገልግሎት በተለያዩ መስኮች እያንዳንዱ ሰው ያለ ትርፍ ፍለጋ እና ያለ ክፍያ ሙያዊ አጋንዖት ለማያውቋቸው ግለሰቦች፣ ጎረቤቶቹ፣ ለማኅበረሰቡ እና በጠቅላላው ለሕዝብ የሚያበረክተው አስተዋጽዖ መሆኑን ያመላክታል፡፡ በኢትዮጵያም የበጎ ፈቃድ አገልግሎት መቼ እና በማን እንደተጀመረ የተጠናከረ መረጃ ባይኖርም የረጅም ጊዜ የአገልግሎት ታሪክ እንዳለው ይታመናል፡፡

ለዚህም ኢትዮጵያዊያን በጦርነት እና በችግር ጊዜ የመረዳዳት እና የመደጋገፍ ልምዳቸው ከፍተኛ ነው፡፡ በተለይ በ1962 ዓ.ም ከውጭ የመጡ ሁለት መቶ 79 አሜሪካዊያን በጎ ፈቃደኛ መምህራን ጽንሰ ሀሳቡ የበለጠ እንዲሰርጽ አድርገዋል፡፡በተደራጀ መንገድም ባይሆን በሀገራችን ሲፈፀም የቆየው የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ከ2003 ዓ.ም ጀምሮ የክረምት እና የበጋ በሚል መርሐግብር ተጀምሮ ዛሬ ድረስ ዘልቋል፡፡ ክልሎችና አገር አቀፍ ማኅበራዊ ድርጅቶች የቀድሞ የቅኝ ግዛት ግዛቶች በኢኮኖሚ እንዲዳብሩ ለመርዳት በጎ ፈቃደኞችን ልከዋል፡፡ እ.ኤ.አ. በ1930 ዎቹ እና 1940ዎቹ ውስጥ፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ወጣቶችን በማሰባሰብ የአደጋ ጊዜ ዕርዳታ እና አዲስ ነፃ ለሆኑ አገሮች የኢኮኖሚ እፎይታ ሲሰጡ የበጎ ፈቃደኞች ካምፖች አደጉ፡፡

**ሐዲስ፡-** በጎፈቃድ አገልግሎት እንደ ኢትዮጵያና አማራ ክልል ያለው ምን ይመስላል?

**እንግዳ፡-** ሀገራችን ኢትዮጵያም በዚሁ መከራው/ ችግሩ ሞልቶ በተረፈባት ምድር ላይ የምትገኝ ይልቁንም የችግር መዓት የተከማቸባት አህጉራችን አፍሪካ ውስጥ ያለች በመሆኗ የበጎ ፈቃድ አገልግሎትን በጥብቅ ከሚሹ ሀገራት አንዷ ነች፡፡

ኢትዮጵያ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት የመስጠት ባህል የነበራትና በፍጹም ወንድማማችነት ዜጎች የሚኖሩባት ችግራቸውን በጋራ በመተባባር የሚያሳልፉባት ሀገር ስትሆን ይህ በመስጠት የሚገለጸው በጎ ፈቃደኝነት የሀገሩ ባህል ልዩ ልዩ ዓይነት ልማድና ወግም የነበረው ሲሆን ሲያዝን የዝን ብሎ ከመስጠት ጀምሮ ሲዘምት የስንቅ፣ ሲመለስ የደስታ፣ ሲሻር የሹመት አይደንግጥ፣ ሲሾም የምስራች፣ ወዘተ. ብሎ እስከ መስጠትም የረቀቀ ነው፡፡ ከምንም በላይ ግን ወርቃማ የነበረው ሲታመሙ የመጠየቂያ ብሎ ከመስጠት ጀምሮ ሲወረስ፣ ሲከስ፣ ሲቃጠልበት፣ ሲቀማ... እርጥባን ብሎ መስጠት የተለመደ ተግባር በመሆኑ ለአረጋውያን፣ ረዳት ለሌላቸው እናቶች ተሰብስቦ በደቦ ማረስ፣ መውቃት፣ ሰብስቦ ከጎተራ መክተቱ በግብርና ኖሮ እዚህ ዘመን ድረስ ለዘለቀው ማኅበረሰብ እንግዳ ነገር አልነበረም፡፡ ካመረተው እህል ከፍሎ ከመስጠት ጀምሮ በጉልበቱ እና በሙያው ለችግረኞች መድረስን የሚያውቅ ሕዝብ ነው፡፡ችግር ያጋጠማቸውን ሰዎች ቀስቃሽ ሳያስፈልግ ማገዝ የበጎ እሴቶቻችን አንድ አካል ነው፡፡ በተለይ በገጠር መንገድና ዘመናዊ የትራንስፖርት አገልግሎት ባልነበረበት ወቅት የታመሙ ሰዎችን በወሳንሳ ተሸክሞ ሩቅ አካባቢ ወስዶ ማሳከም የታማሚው ቤተሰቦች ብቻ ሳይሆኑ የሀገሬው/ የአርሶ አደሩ ድርሻ ነበር፡፡ሙታንን መቅበርም እንደዚያው፡፡ ሕዝብ ተባብሮ የቀብር ጉድጓድ ቆፍሮ፣ አስከሬን ተሸክሞ የቀብር ሥነ-ስርዓቱን ይፈጽማል፡፡ በኢትዮጵያ ሙታንን መቅበር እንደ ሌላው ዓለም የቤተሰብ እዳ ሆኖ አያውቅም ምክንያቱም ማህብረሰቡ የጋራ ኃላፊነት የሚወስድባቸው እጅግ በርካታ ጉዳዮች አሉት ፡፡ እንደ አሁኑ የአእምሮ ሕሙማን ማሰባሰቢያ ሳይደራጅ፣ መንግሥታዊ እና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ሳይገቡበት አካል ጉዳተኞችን እና የአእምሮ ህሙማንን መንከባከብ የጋራ ድርሻ ነበር፡፡

ኢትዮጵያውያን የበጎ ፍቃድ አገልግሎት የሚሰጡት በችግር ወቅት ብቻ ሳይሆን ከላይ አስቀድመን እንደ ጠቀስነው በምርትስራ ላይም በበጎ ፍቃድ አገልግሎት ይተጋገዙ።የደቦ ባህልን ለዚህ ማሳያነት መጥቀስ ይቻላል። ከቤተሰብ አቅም በላይ የሆነ የምርት ስራ ለምሳሌ እርሻ፣ አጨዳ፣ ጎጆ ማዋቀር... ሲኖር መንደርተኛው በሙሉ የራሱን መሳሪያ ይዞ በስራ ይተባበራል። ለዚህ መልካም ግብር የሚያዘነበል ሥነ ልቦናም ኢትዮጵያውያን በግላቸው ብቻ ሳይሆን ለበጎ ነገር በበጎ ፈቃድ በሀገር መሪዎች ጥሪ መዝመትንም ያውቁበታል። የበጎ ፈቃድ አገልግሎት በተለይ በክፉ ቀናት እጅግ ወሳኝ ሚና ይጫወታል። በንጉሠ ነገሥት ምኒልክ ዘመን ተከስቶ በነበረው ክፉ ቀን በተባለው ብዙ እንስሳት ባለቁበት ዘመን አርሶ መብላትም ሆነ ዘርቶ መቃም ጭንቅ ነበር። የከብቱ ማለቅ ለሰው ማለቅ ተረፈ። በዚህ ጊዜ መላ የዘየዱት ንጉሠ ነገሥቱ የበጎ ፈቃድ አገልግሎትን በአርአያነት ማሳየት ነበር። መኳንንቱም መሳፍንቱም እርሳቸውን አይተው ወርደው ሕዝቡን እንዲያገለግሉ ለማድረግ ጥረት አደረጉ። ንጉሡ እጅና እግራቸው በአሾህና ጋሬጣ እስኪደሙ እና እስኪቆስሉ ከእንጦጦ ማርያም በታች ያለውን የኤካን ጫካ ሁሉ ለማልማት ጥረው ነበር። በእርግጥም ትልቅ፣ ትንሽ፣ ቄስ፣ መነኩሴ ሳይል በሀይማኖት ሳይከፋፈል ሁሉም ተሳትፎ የሚገባውን ያደረገበትን የዚያን የክፉ ቀን ዘመቻ ዘመናዊ የሆነውን የበጎ ፈቃደኞች አገልግሎት የበለጠ ባህል ለማድረግ በስፋት የተንቀሳቀሰበት ጊዜ ነበር።

ዓለም አቀፍ በጎ ፈቃደኛ ወገኖችም ሀገራችንን በመጎብኘት በህክምና እና በትምህርት መስክ ይሰጡ የነበረው አገልግሎት ለኢትዮጵያውያን ዘመናዊ በጎ ፈቃድ አገልግሎት ማደግ ብርቱ ተሞክሮዎች ነበሩ።

በወታደራዊው ደርግ የስልጣን ዘመን ደግሞ ምንም እንኳን የተወሰነ አስገዳጅነት ቢኖረውም በ1967 ዓ/ም የሁለተኛ ደረጃና የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን የተሳተፉበት የእድገት በህብረት ዘመቻ እንደ በጎ ፍቃድ አገልግሎት ልምምድ የሚታይ ነበር ላለፉት በርካታ ዓመታት በሀገራችን ይደረጉ የነበሩ የወጣቶች የበጎ ፈቃድ አገልግሎቶችም ልማታዊ ሥራዎችን ከማስፋፋት አንጻር ከፍተኛ አስተዋጽኦ ነበራቸው።

በአብዛኛው የማጠናከሪያ ትምህርት በመስጠትና በመንገድ ትራፊክ ቁጥጥር ሥራዎች ላይ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ሲያደርጉ ከ2010 የክረምት ወራት ጀምሮ እጅግ በተለየ መንገድ በፖሊሲ የሚመራ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት እንዲስፋፋ በክቡር ጠቅላይ ሚኒስትሩ አማካኝነት ሰፋፊ ዘመቻዎች ተጀምረዋል። የአረጋውያንን ቤቶች በመጠገን ፣ ችግረኛ ተማሪዎችን በመርዳት ፣ ደም በመለገስ ወዘተ ራሳቸው ጠቅላይሚኒስትሩ የጀመሯቸውን የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ሥራዎች ሌሎች የማኅበረሰቡ ክፍሎችም ተከትለው ለማስፋፋት ችለዋል የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ኤጀንሲም የበጎ ፍቃድና በጎ አድራጊነትን ባህል ማድረግ የሚል ስልጣን በአዋጅ ከተሰጠው ጊዜ አንስቶ በርካታ መዋቅራዊ ፣ የግንዛቤና ንቅናቄ እንዲሁም ስርዓት ዝርጋታ ስራዎችን በመስራት ላይ ይገኛል፡፡

**ሐዲስ፡-** የበጎ ፈቃድ አገልግሎቶች የሚባሉ ምን ምን ናቸው ? እያዳንዳቸውን ቢያብራሩልኝ?

**እንግዳ፡-** በ2017 በጀት አመት በ17 የስራ መስኮች የሚተገበር ሲሆን የስራ መስኮችም የአረንጓዴ አሻራ መርሐ-ግብር ፤ የቤት እድሳትና ግንባታ፤ ለችግር የተጋለጡ የህብረተሰብ ክፍሎችን መደገፍ፤ የግብርና ልማት ስራዎች ፤ ኢትዮ ኮደርስ ስልጠና፣ ገጠር ኮሪደር ልማት ፣ ከተማ ኮሪደር ልማት፣ የትምህርትና ስልጠና አገልግሎት ፤ የጤና አገልግሎት፤ መሰረተ ልማቶችን ማጠናከር እና ማልማት ፤ የወጣቶች ሰላምና ደህንነት ፤ የመንገድ

ደህንነት እና ትራፊክ አገልግሎት፤ የአካባቢ ጥበቃና እንክብካቤ ፤ የትውልድ ግንባታ አገልግሎት ፤ የስርዓተ ፆታ እኩልነት እና ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን መከላከል ህገ-ወጥ የሰዎችን ዝውውርንና ማህበራዊ ጠንቅ ተጋላጭነትን መከላከል ፤ የሙያ አገልግሎቶችና መረጃ ናቸው፡፡

**ሐዲስ፡-** በእነዚህ ዘርፎች አፈፃፀሙ ከባለፉት አመታት ጋር ሲነፃፀር ምን ይመስላል?



*በአረንጓዴ አሻራ በጎ ፈቃድ አገልግሎት ወጣቶች በንቃት ሲሳተፉ የሚያሳይ ምስል*

**እንግዳ፡-** የ2017 ዓ.ም አፈጻጸም ከባለፉት አመታት ጋር ሲነጻጸር በስራ መስክ፣ በበጎ ፈቃድ ተሳትፎ፣ የህብረተሰቡ ድጋፍና ትብብር፣ የአመራር ቁርጠኝነትና ድጋፍ የተሻለ ነው ብሎ መውሰድ ይቻላል፡፡ በመገለጫ ለማሳየት ያህል ባለፉት አመታት ከ17 ባነሱ የስራ መስኮች አገልግሎቶች ተከናውነዋል፡፡ በተጨማሪም አዳዲስ የአረጋውያን ቤቶች ተገንብተዋል፡፡ ከተሳትፎ አንጻርም በቁጥር ደረጃ ብልጫ ያለው ተሳትፎ ተመዝግቧል፡፡ አመራሩም በተሻለ ቁርጠኝነትና ድጋፍ አድራጊነት የተለያዩ የበጎ ፈቃድ አገልግሎቶች እንዲከናወኑ ትኩረት ሰጥተው እስከማስፈጸም ድረስ ተረባርበዋል፡፡

**ሐዲስ፡-** በ2017 በጀት አመት ወጣቱን በጎ ፈቃድ አገልግሎት ስራ ለማሳተፍ የተያዘው እቅድ ምን ያህል ግቡን መቷል? ካልተሳካ ለምን? በእስካሁኑ ምን ያክል ተፈፃሚ ሆኗል?

**እንግዳ፡-** ባለፉት ዓመታት ይሰራበት እንደነበረው ዘንድሮም በርካታ ወጣቶችና ዜጎች ተሳትፈውበታል፡፡ በዚህ አመት ከእቅዱ በላይ የተፈጸመበት አመት ነው፡፡ አጠቃላይ የተሳተፉት ዜጎች 9.853296 በጎ ፈቃደኛ ዜጎች ሲሆኑ ከዚህ ውስጥ 53089.56 ወጣቶች በበጎ ፈቃድ አገልግሎት ስራ መሰማራት የቻሉበት ወቅት ነበር፡፡ በድግግሞሽ ከ56 ሚሊዮን በላይ ዜጎች ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡ ከ25 ቢሊየን ብር በላይ የሚሆን ወጭ ማዳን ተችሏል፡፡

**ሐዲስ፡-** በየሴክተር መስሪያ ቤቶች እየተከናወነ ያለው የአቅመ ደካማ ቤት ግንባታ ጥገና አፈፃፀሙ እንዴት ይገለፃል? የበጀት ምንጩ እንዴት ተጣጥሞ እየተመራ ነው?

**እንግዳ፡-** 5ሺ 971 አረጋውያን ቤት በአዲስ መገንባት ተችሏል፡፡ 11915 አረጋውያን ቤት በነባር መጠገን ተችሏል፡፡ ይህ በበጋ በጎ ፈቃድ አገልግሎትም ተጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል፡፡



በበጎ ፈቃድ አገልግሎት የታደሰ ቤትን የሚያሳይ ፎቶ ትናንትና ዛሬ



የበጎ ፈቃድ አገልግሎት በደም ልገሳ መስክ ሲፈጸም የሚያሳይ ፎቶ

ይህ ሁሉ የበጎ አድራጎት የበጀት ምንጭ ከህብረተሰቡና ከበጎ ፈቃድ ድርጅቶች የተገኘ ነው፡፡

**ሐዲስ፡-** በጤናው ዘርፍ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ምን ይመስላል? አገልግሎት የሚሰጣቸዉ የህብረተሰብ ክፍሎች የትኞቹ ናቸው? ለምን?

**እንግዳ፡-** በጤናው ዘርፍ የተከናወኑ ተግባራት የደም ልገሳ በጤና ተቋማት፤ የህክምና መገልገያ ድጋፍ ማድረግ፡፡ በተዋልዶ ጤና አገልግሎት ግንዛቤ መስጠት፤ የወባ ትንኝ መራቢያ ቦታዎችን ማጽዳት፤ የጤና ተቋማት እድሳት፤ በቤት ውስጥ የህክና ድጋፍ ፤ የጤና ፓኬጅ ግንዛቤ መፍጠር እና ሌሎችም ተግባራት ተከናውነዋል፤ ለአብነት ደም መለገስ ወስደን ስንመለከት 23296 ዩኒት የደም ልገሳ ስራ ተሰርቷል፡፡ ደም መለገስ የአንድ ፍጡር ሰው ህይወት ማዳን በመሆኑ አብዛኛው አፈጻጸም የወጣቶች ድርሻ ከፍተኛ ቢሆንም ተግባሩ ግን ሁሉም የህብረተሰብ ክፍሎችና ያሳተፉ ነበር፡፡

**ሐዲስ፡-** በጎ ፈቃድ አገልግሎት መስጠት የሚገደብባቸው ጉዳዮች ይኖሩ ይሆን? ካለ ለምን?

**እንግዳ፡-** የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ዕድሜ እና ፆታ፣ ማኅበራዊ ደረጃ፣ መልካ ምድራዊ አቀማመጥ ሳይገድበው የሰብዓዊነት መርህን ብቻ መሠረት በማድረግ የሚሰጥ ወይም የሚከናወን ተግባር ነው። በጎ ፍቃድ አገልግሎት ማለት ተሳታፊዎች በፍቃደኝነት ላይ የተመሰረተ ተሳትፎ በማድረግ ውስጣቸው ከሚሰማቸው ሰብአዊ አመለካከት ተነስተው ለማኅበረሰቡ ሰፊ የልማት አውታሮችን በመዘርጋት የዜግነት ኃላፊነትን የሚገነዘቡ ሀገራዊ እና ብሔራ ግዴታዎችን የሚያውቁበት፣ በማኅበራዊ ሚናዎች ስር ግንባር ቀደም የሚሆኑ፣ የሀገር እና የወገን ፍቅርን የሚያዳብሩበት ትልቅ ሚና ያለው ተግባር ነው። በጎ ፍቃድ የሚሠሩ ወጣቶችም የእረፍት ጊዜያቸውን ተጠቅመው ልማትን ለማምጣት ለአካባቢ ደህንነት በነጻ ጊዜያቸውን፣ ገንዘባቸውን ፣ ጉልበታቸውን እና ዕውቀታቸውን ከማዋል በተጨማሪ በጎ አመለካከትን የሚያሰርፁበት ተግባር ነው፡፡




*የመንግስት ተቋማት በበጎ ፈቃድ አገልግሎት የትምህርት ቁሳቁስ ሲሳተፉ የሚያሳይ ፎቶ*

**ሐዲስ፡-** በጎ ፈቃድ አገልግሎት በትምህርት ዘርፍ ያለው አፈፃፀሙ ምን ይመስላል? የታዩ ጥንካሬ እና እጥረቶች ምንድን ናቸው?

**እንግዳ-** ትምህርት የአንድ ሀገር እድገትና የጀርባ አጥንተ መሰረት በመሆኑ በክረምት በጎ ፈቃድ አገልግሎት በርካታ ስራዎች ተከናውነዋል፡፡ የማጠናከሪያ ትምህርት፣ 493806 92683 ፓኮ እስክርቢቶ፣ 50000 ሺ ቦርሳ እና የማጠናከሪያ ትምህርት አገልግሎት፤ የተግባር ተኮር የመሰረተ ትምህርት አገልግሎት መስጠት፤ የትምህርት ቁሳቁስ ማሰባሰብ፤ ለአካል ጉዳተኞች ድጋፍ ማድረግ፣ የተማሪ ቅስቀሳና ምዝገባ፤ የትምህርት ቤቶች ጥገና፤ የኪነ ጥበብ ስልጠና፤ መሰረታዊ የኮመፒውተር ስልጠና ስራዎች በክረምት ተከናውነዋል፡፡ 82579 ዩኒፎርምና የትምህርት ቁሳቁስ ማሰባሰብ ተችሏል፡፡ በየደረጃው ተግባሩ ተይዞ ለማጠናከር የተከናወነ ነው፡፡ በጎ ተግባሩን የበለጠ ለማጠናከር በትጋት እየተሰራ ነው፡፡

**ሐዲስ፡-** የበጎ ፈቃድ አገልግሎቶች ድርጅቶች ጥምረት መኖር ቅንጅታዊ አሰራር ለማምጣት ያለዉ ፋይዳ ምን እንደሆነ ቢገልጹልኝ?

**እንግዳ፡-**ጥምርቱ ሰባዊነት ከማበረታታት አኳያ ትልቅ አስተዋጾ አለው፡፡ በተለይ ወጣቱ የተጓዱ ህብረተሰብ ክፍሎችን መርዳት እዲችል አንዱ የማነሳሻ መንገድ ነው፡፡ ሌላው የወጣቱን ስብዕና ለመቅረጽ ዝቅ ብለው ለሀገራቸውና ለወገናቸው እዲያገለግሎ የስራ ባህልን እንዲያዳብሩ ከማስቻሉ ባለፈ የሀገራቱን ህዝብ አብሮነትና አድነት ያጠናክራል፡፡

**ሐዲስ፡-** የህብረተሰቡ የበጎ ፈቃድ ፍላጎት እንዲጨምር ምን መደረግ አለበት ይላሉ?

**እንግዳ፡-** የክልሉ በጎ ፈቃድ አገልግሎት ጠቀሜታውና አበርክቶው ሰፊ በመሆኑ ወጣቶች በያሉበት ከአስተባባሪ ተቋሙ ጋር በመሆን የተጀመረውን አግልግሎት አጠናክረው እንዲቀጥሉ ማድረግ እና አጋር ተቋማትም ከበጎ ፈቃድ ሰጭ አካላት ጎን በመሰለፍ ተግባሩ እንዲጠናከር ድጋፍ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ የተቋሙ አመራር፣ ባለሙያው እና አደረጃጀቶች በጋራ ተቀናጅቶ መስራት አለባቸው፡፡ ማህበረሰቡን ማሳተፍና ባለቤት ማድረግ፡፡ወጣቱና ህብረተሰቡ ትምህርትና ሰልጠና እንዲወስዱና ወደ ሌሎች እንዲተላለፍ የሚዲያ ሽፋን በተገቢው መንገድ መስራት እና አገልግሎቱ የተቸገሩትን ከመርዳት ባለፈ በጎ ምኞትን ተላብሰው ከማኀበረሰባቸው ጎን ሆነው የሚያውቁትን የሚያስተምሩበት እና ከሌሎች አካላትም የሕይወት ክህሎት የሚቀስሙበት ዋነኛ መንገድ ነው።

የወጣቱን ማኀበራዊ ተሳትፎ ለማበረታታት፣ ለማሳደግ እና ዕምቅ አቅሙን ለመጠቀም፣ለሕፃናት እና ለታዳጊ ወጣቶች አርዓያ (ሞዴል) የሚሆን ትውልድ ለማፍራት፣ በመንግሥት እና በኅብረተሰቡ ያልተሸፈኑ የልማት ፍላጎቶችን ለማሟላት፣ ለኅብረተሰቡ ተቆርቋሪ እና የኃላፊነት ስሜት የሚሰማው ዜጋ በማፍራት ከአልባሌ ቦታዎች ርቀው ኅብረተሰቡን ሊጠቅሙ በሚችሉ የሥራ መስኮች የሚሰማሩበትን ዕድል ነው ።

በተጨማርም የዜግነት ኃላፊነትን እንዲገነዘቡ፣ ሀገራዊና ብሔራዊ ግዴታቸውን እንዲያውቁና በማህበራዊ ሚናዎቻቸው ውስጥ ግንባር ቀደም ሆነው የሀገርንና የወገንን ፍቅር የሚያዳብሩበት ሁኔታ ለመፍጠር ብሎም ዓለማዊ ተግዳሮቶችን ተቋቁመውና ጠንካራ የሥራ ፍላጎት አዳብረው ራዕያቸውን ማሳካት የሚችሉ ወጣቶችን ለማፍራት የሚረዳ ተግባር ነው ።

**ሐዲስ፡-** ስራዎች ሲሰሩ ያጋጠሙ ተግዳሮቶች ምን ምን ነበሩ?

**እንግዳ፡-** በወቅቱ ስራዎችን ስናከናውን ያጋጠሙን ችግሮች ፤ የክትትልና ድጋፍ ማድረጊያ በጀት እጥረት፤ በወረዳ ደረጃ መረጃ የመለዋወጫ ኢንተርኔት መቆራረጥ እና አንዳንዴ የአጋር ተቋማት የቅንጅት ስራዎች መጓደል በመጠኑም ቢሆን አጋጥሟል፡፡

**ሐዲስ፡-** የበጎ አድራጎት ስራዎች ለማስፈፀም ከማን ምን ይጠበቃል?

እንግዳ፡- ከወጣቶች ትጋትና ቁርጠኝነት መኖር አለበት፡፡ ቢሮው የማስተበበር ስራውን መስራት አለበት፡፡ ወጣቶች በተመደቡበት የስራ መስክ እና በተሰጣቸው ተልዕኮ መሰረት ተግባራትን በጊዜና በጥራት ማከናወን ይኖርባቸዋል፡፡ ይህ ከሆነ የማንሻገረውና የማናልፈው መሰናከል አይኖርም፡፡ አጋር አካላት የበጎ ፈቃዱ ስራ ማሳለጫ የሚሆኑ የቁሳቁስ ፣ የገንዘብና የሙያ ድጋፍ ማድረግ ሌላው በየደረጃው ያለው አስተባባሪ ተቋም ተግባራት በተቀመጠላቸው ጊዜ ገደብ ተግባራትን እየተፈጸሙ ስለመሆናቸው ሪፖርት በማጠናከርና ግብረ መልስ በመስጠት እየገመገሙ መምራት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

**ሐዲስ፡-** ቀረየሚሉትን ተጨማሪ ሀሳብ ካለዎት ቢገልፁልን?

**እንግዳ፡-** የክልሉ መንግስት የ25 ዓመት አሻጋሪ እቅድ አቅዶ ወደ ተግባር ገብቷል፡፡ ስለሆነም ይህ እቅድ ለወጣቶች እንደሆነ ግንዛቤ ማስጨበጥ ያስፈልጋል፡፡ ይህ ተግባር በክልሉ ውስጥ እንደ ባህል ተደርጎ ተወስዷል፡፡ ተግባሩም በስኬት ተጠናቋል፡፡ ይህ የሆነበት የስኬት ምስጢር ደግሞ ቅንጅታዊ አሰራሩ የተሻለ በመሆኑ እና አመራሩ ለተግባሩ የሰጠው ትኩረት ነው፡፡ በተለይ የክልሉ ርእሰ መስተዳድርና አስተባባሪዎችን ማመስገን እፈልጋለሁ ከመክፈቻው ጀምሮ እየገመገሙ በመምራት የሰጡት ትኩረት የሚያስመሰግን ነው፡፡

በየደረጃው ያሉ የዞን አስተዳዳሪዎች እና ከንቲባዎች፤ በየደረጃው ያሉ የፓርቲ መዋቅር በየደረጃው ያለው ስትሬንግዝ ቴክኒክ ኮሚቴዎች ተመዝግበው በጎ ፈቃድ አገልግሎት የሰጡ ዜጎችን አጠቃላይ ማህበረሰቡን የወጣትና የሴት አደረጃጀቶችን በየደረጃው ያሉ የተቋማት ባለሙያዎችን የሚድያ ተቋማትን እያመሰገንኩ ከስሙ ተነስተን ቀለል አድርገን እንደሚገለጸው በጎነት ለኢትዮጵያ ከፍታ በሚል እየሰራን በጎ ብለን ስናስብ በርካታ ነገሮች አሉ ለአብነት መታዘዝን፤ መረዳዳትን ና መተጋገዝን እንዲሁም የነፍስ ማዳን ስራ ነው፡፡

የሚጠቅም ስራ ሰለሆነ የኛን እናትና አባቶች የሚደግፍ ሲሆን ለኛም ፀጋም ዕድልም ከመሆኑ ባሻገር ለራስ የህሊና እረካታ ከመስጠቱም በላይ ተጠቃሚ እንሆናለን፡፡ ለዚህ ደግሞ ሁሉም የክልሉ ማህበረሰብ ይህን በጎ ተግባር በመደገፍ የድርሻውን እንዲወጣ ስል መልእክት አስተላልፋለሁ፡፡

እኛም በጎነት መልካምና ይበል ሊባል የሚገባው ጥሩ ባህላችን እንደሆነ እየደገፍን የአዕምሮ እርካታና የመንፈስ ጥንካሬ የሚገኘው ተባብሮና ተረዳድቶ ችግርን በጋራ ማለፍ ሲቻል ነው እንላለን፡፡ ለወገን ደራሽ ወገን ነው በጎ መስራትን ባህላችን እናድርግ የዝግጅት ክፍሉ መልዕክት ነው - **ሰላም!**

## ከፎቶ ማህደር



AM-MESOB

መሶብ የአንድ ማዕከል አገልግሎት ሰራተኞች(ባህርዳር)



የ25 ዓመት አሻጋሪ የልማት እቅዱ ዙሪያ ከከፍተኛ አመራሩ ጋር የተደረገ ዉይይት

# ከፎቶ ማህደር









የባህርዳር ከተማ አስተዳደር የኮሪደር ልማት ጉብኝት




የህዳሴው ግድብ መጠናቀቅን አስመልክቶ የተደረገ የድጋፍ ሰልፍ (ባህርዳር)





